
# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 227 ሚያዝያ 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

## አቶ ደመቀ መኮንን በአራት የአፍሪካ አገሮች የሚያደርጉትን ጉብኝት በታንዛኒያ ጀመሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ክቡር የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በአራት የአፍሪካ አገራት የሚያደርጉትን ጉብኝት በታንዛኒያ ጀመሩ።

ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በታንዛኒያ፣ ኮሞሮስ፣ ቡሩንዲና ዩጋንዳ የሚያደርጉትን ጉብኝት ለመጀመር ትናንት ታንዛኒያ ገብተዋል።

ክቡር አቶ ደመቀ ከታንዛኒያ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳሚያ ሳሉሁ ጋር የህንድ ውቅያኖስ ከተማ በሆነችው በዛንዚባር በሁለትዮሽና አካባቢያዊ ጉዳዮች ውይይት አድርገዋል።

አቶ ደመቀ መኮንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ወቅቱን የዋጀና የአመራር ጥበብን የተላበሰ አመራር ለማፍራት እየተሰራ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ወቅቱን የዋጀና የአመራር ጥበብን የተላበሰ አመራር ለማፍራት እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ።

በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ የፕሮግራም ዘርፍ ምክትል ርዕሰ አካዳሚ ወይዘሮ ህይወት አለማየሁ አካዳሚው አመራሩን ወደ ልህቀት ይወስዳል የተባለ ስልጠና ትናንት ሲጀመር እንደገለጹት፤ ውጤታማ አመራር ለመፍጠር ስልጠና ወሳኝ ነው።

እየተሰጠ ያለው ስልጠና በመንግስት፣ በግልና በአካዳሚው ውስጥ ላሉ ከፍተኛ አመራሮችና በፖለቲካው መስክ ላሉ አመራሮች ጭምር መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ርዕሰ አካዳሚዋ፤ ወቅቱን የዋጀና የአመራር ጥበብን የተላበሰ አመራር ለማፍራት እየተሰሩ ካሉ ስራዎች አንዱ ስልጠና መሆኑን ተናግረዋል።

የስልጠናው ዋና ዓላማ አመራሮችን ወደ ልህቀት መውሰድ መሆኑን የገለጹት ምክትል ርዕሰ አካዳሚዋ፤ የሚሰጠው ስልጠናም በተለያዩ የኃላፊነት ቦታ ላይ የሚያገለግሉ አመራሮች በተሻለ እውቀትና ክህሎት ህዝቡንና ተቋማቸውን እንዲመሩ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

ወቅቱን የዋጀና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ገብረመስቀል ጫላ

## ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከወጪ ንግድ ሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር ተገኘ

**በኃይሉ አበራ**

አዳማ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከወጪ ንግድ ሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ኢፕድ እና ኢቢሲ

### በጋራ መስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- አንጋፋዎቹ የሚዲያ ተቋማት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በጋራ መስራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራረሙ።

የመግባቢያ ሠነድ ፊርማውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጥናትና ምርምር ፣ አቅም ግንባታና ገበያ ልማት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ሔለን እስክንድር እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብዱራህማን ኑቤ ተፈራርመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ሔለን እስክንድር በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ አንጋፋ ተቋማቱ የሀገርን ታሪክ የያዙ በመሆናቸው አቅማቸውን በጋራ በመጠቀም ለትውልዱ የሚጠቅም ሥራ በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን የሚረዳ ስምምነት ተፈጽሟል ብለዋል።



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

ኢፕድና ኢቢሲ በተለያዩ ጊዜያት ስራዎችን በትብብር ሲያከናውኑ ቆይተዋል ያሉት ወይዘሮ ሔለን፣ በስምምነቱ መሰረት ደግሞ ስራዎቻችንን በተሻለ አግባብ ለማከናወንና ትብብሩን ላቅ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ ያግዛል ሲሉ ገልጸዋል።

ኢፕድ እና ኢቢሲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ቢሮው በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያለው ድጋፍ አደረገ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**




አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በከተማው ከሚገኙ የትምህርት ማህበረሰብ አባላት ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ቦታዎች በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሚውል ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያለው የዓይነት ድጋፍ አደረገ።

ቢሮው ከትምህርት ማህበረሰቡ ጋር በጋራ የተሰበሰበው 13 የዓይነት ድጋፍ የጫኑ መኪናዎች ለኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ጽህፈት ቤት አስረክቧል።

ድጋፉን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ ር) ለኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ጽህፈት ቤት የኮሙኒዩኬሽን ኃላፊ ወይዘሮ ኤልዳና ሱሊማን አስረክበዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ርክክቡ በተደረገበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ድጋፉ ከአስተዳደርና ሰራተኞች፣ ከወላጆች፣ ከተማሪዎች እንዲሁም ከመምህራን በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች የተሰበሰበ ነው ብለዋል።

በተለይ የትምህርቱ ማህበረሰብ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ ማድረጉ ችግሩን ከመቅረፉም በተጨማሪ አዲሱ ትውልድ የመደጋገፍ፣ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት እንዲሁም አካፋይነት ባህልን እንዲያጎለብትና ግንዛቤ እንዲጨብጥ ያግዛል ብለዋል።

የተደረገው ድጋፍ ምግብና ምግብ ነክ ቁሳቁሶች፣ የተለያዩ አልባሳትና የከብቶች መኖን ያካተተ ነው ያሉት ዶክተር ዘላለም፤ተማሪዎች ካላቸው የእለት ጉርሳቸው ላይ ቀንሰው መስጠታቸው ለተጎዱ ወገኖቻቸው ያላቸውን አጋርነት ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፣ ድጋፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለን የማካፈልና የመረዳዳት እንዲሁም የመተሳሰብ ባህል እያደገ የመምጣቱ ማሳያ ነው፤ ይህም የበለጠ እንዲያድግና ተጠናክሮ እንዲቀጥል መስራት ያስፈልጋል።

በመጨረሻም የወገኖቻቸውን ችግር ለመቅረፍ ካላቸው ላይ ቀንሰው ላካፈሉ የትምህርት ማህበረሰብ አባላትና ጉዳዩ እንዲሳካ ትብብርና ድጋፍ ላደረጉ አካላት ምስጋና አቅርበዋል።

ድጋፉን የተረከቡት የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ጽህፈት ቤት የኮሙኒዩኬሽንና ዓለም አቀፍ ትብብር ኃላፊ ወይዘሮ ኤልዳና ሱሊማን በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮና የትምህርቱ ማህበረሰብ በክልሉ በአንዳንድ አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ ምክንያት የተጎዱ ዜጎችን ለመደገፍ ላሳዩት ቁርጠኝነትና አብሮነት ምስጋና ያቀረቡ ሲሆን፤ ድጋፉን ለሚመለከታቸው አካላት እንደሚያደርሱ ተናግረዋል።

ድጋፉ በድርቁ አካባቢ ከምግብና ከጤና ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን ችግር የሚቀርፍ እንዲሁም ዜጎችን በስነ ልቦና ራሳቸውን በዘላቂነት እንዲያቋቁሙ ተስፋ የሚሰጣቸው ነው ያሉት ወይዘሮ ኤልዳና፤ ከዚሁ ጎን ለጎን የህዝቦች ለህዝቦችን መልካም ግንኙነት የሚያጎለብትና ችግሮችን በጋራ በመደጋገፍ እንዴት መሻገር እንደሚቻል የሚያሳይ መልዕክት ያዘለ ነውም ብለዋል።

ኃላፊዋ አክለውም፣ በድርቁ ምክንያት አስቸኳይ የምግብና የጤና ርዳታ የሚፈልጉ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ ያሉ ሲሆን፤ ጽህፈት ቤቱ ጊዜአዊ እርዳታ ማሰባሰብ ብቻ ሳይሆን ዜጎችን በዘላቂነት ለማቋቋም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በትኩረት እየሰራ ነው ብለዋል።

# “ሰላምን ለማጽናት ከፌዴራል መንግስት ጋር ያለንን ግንኙነት የበለጠ አጠናክረን እንሰራለን”

**- አቶ ጌታቸው ረዳ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት**

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- ሰላም እንዲጸና ሁላችንም ከፌዴራል መንግስት ጋር ያለንን ግንኙነት የበለጠ አጠናክረን እንሰራለን ሲሉ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳ ተናገሩ።

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በመንግሥትና ሕወሓት የሰላም ስምምነት የመጣውን ውጤት ተከትሎ «ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና» በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ወዳጅነት ፓርክ የእውቅና እና ምስጋና መርሃ ግብር ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት አቶ ጌታቸው ረዳ፤ ከፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት በኋላ ህዝቡንና ክልሉን ተጠቃሚ የሚያደርጉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል ብለዋል።

ጦርነት አብቅቶ ሰላም እንዲጸና ሁላችንም ጥረት እናደርጋለን፤ ከፌዴራል መንግስት ጋር ያለንን ግንኙነት የበለጠ እናጠናክራለን፤ ሌሎች ክልሎችም ይህንን ሊሰሩ ይገባል ሲሉም አክለዋል።

ሰላምን ማጽናት የእያንዳንዱን ሰው ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ እስካሁን የተሰሩ ስራዎች የሚደነቁ ናቸው ብለዋል። በተለይ ደግሞ ስምምነቱ በፍጥነት ተግባራዊ እንዲደረግ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ላሳዩት ከፍተኛ ድፍረት የተሞላበት ቁርጠኝነት አመስግነዋል።

ከዚህ በኋላም የድፍረት ውሳኔዎች መቀጠል እንዳለባቸው እና ቀሪ ስራዎች በተያዘው ፍጥነት ልክ መቀጠል እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ከትግራይ ህዝብ የፍቅርና የሰላም መልዕክት ይዤ መጥቻለሁ ያሉት አቶ ጌታቸው፤ የትግራይ ህዝብ ጦርነት ሰልችቶታል፤ በዚህም ያገኘው ሰላም ወደኋላ እንዲመለስ ፈጽሞ አይፈቅድም ብለዋል።

ለስምምነቱ የተባበሩትን ሁሉ ያመሰገኑት አቶ ጌታቸው፤ በቀጣይ ሂደት ውስጥ የመተማመን መንፈስና ሰላምን የማጽናት ስራ የራሳችን ቢሆንም፤ ወደፊት በሀገራችን የጠፉ ማህበረሰቦችን ለመፈለግ፣ የፈራረሱ ተቋማትን ለመገንባት እና በሀገራችን ፍትህ ለማስፈን በምናደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ በአፍሪካዊ የወንድማማችነት መንፈስ ከጎናችን እንደምትሆኑ እምነቴ ነው ብለዋል።

ፖለቲከኞች የሰላም ቋንቋ ማውራት መቻል አለብን ያሉት አቶ ጌታቸው፤ መርዝ የተፉ አንደበቶች ሰላምና ፍቅርን መስበክ ሊጀምሩ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

# ሊጉ በሰው ተኮር ፕሮጀክቶች ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ገለጸ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዳማ፡- የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ቀርጾ ወደ ተግባር በገባባቸው ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች ላይ ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገቡን የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ አሰለፈች ታደሰ ተናገሩ።

ኃላፊዋ የሊጉን የዘጠኝ ወር የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በአዳማ ከተማ ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፣ በሌማት ትሩፋት፣ የአረጋውያን ቤት እድሳት፣ የተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ማሟላት እንዲሁም የክረምት በጎ አድራጎት ንቅናቄዎች ላይ አበረታች ውጤት ታይቷል።

እንደ ወይዘሮ አሰለፈች ገለጻ፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ተሟልቶላቸው ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፤ እንዲሁም አንድም እናት በወሊድ ምክንያት ደም አጥታ አትሞትም በሚል በተለያዩ ጊዜያት ከ20 ሺ. ዩኒት በላይ ደም አሰባስቧል።

በአረንጓዴ አሻራ ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኝ ተተክሏል ያሉት ወይዘሮ አሰለፈች፣ ከ12 ሺ. በላይ ቤት እድሳትና ከአንድ ሺ. በላይ አዲስ ቤት ሰርተን ለአቅመ ደካሞችና ለአረጋውያን እንዲሰጥ አድርገናል ብለዋል።

ኃላፊዋ አክለውም፤ የሴቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በህብረት ስራ እንዲሰማሩ፣ በሌማት ትሩፋት እንዲሳተፉ እንዲሁም የቁጠባ ባህልን እንዲያጎለብቱ ተደርጎ 730 ሚሊዮን ብር ተቆጥቧል፤ ይህም የሴቷን የኢኮኖሚ ጥገኝነት የሚያስቀር ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከሴቶች የስራ እድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ543 ሺ.143 ሴቶች የስራ እድል ተፈጥሯልም ብለዋል።

ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሴቶች የጤና መድን ኢንሹራንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ከ634 ሺ. 690 በላይ ሴቶች ተግባር ተኮር የትምህርት እድል እንዲያገኙ ማድረግ መቻሉን የጠቆሙት ወይዘሮ አሰለፈች፤ ለ98 ሺ. 402 ሴቶች የማህፀን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ምርመራ እንደተደረገም ገልጸዋል።

በተጨማሪም የሴቶችን የመረጃ ልውውጥ ለማጎልበትና በማህበራዊ ሚዲያው የሚገኘውን ክህሎት ለማሳደግ ታልሞ አጫጭር ስልጠና በመስጠት ውጤት ማግኘት ተችሏል ሲሉም አስረድተዋል።

የቤንሻንጉልጉምዝ ክልል ምክትል አፈጉባዔና የክልሉ የብልጽግና ሴቶች ሊግ ስራ አስፈጻሚ ወይዘሮ አለምነሽ ይባስ በበኩላቸው፤ በክልሉ ሊጉ በቀረጻቸው ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ መገኘቱን ጠቁመዋል።

እንደ ወይዘሮ አለምነሽ ገለጻ፣ በክልሉ በሌማት ትሩፋት፣ በስራ እድል ፈጠራ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትና የሴቶች የኃይል ጥቃት ከመቀነስ አኳያ እንዲሁም የሴቶችን አመራርነትና ውሳኔ ሰጪነት በማሳደግ ረገድ ተጨባጭ ለውጥ ታይቶበታል።

# ኢንተርፕራይዙ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተቋማዊ መዋቅር እንዲዘረጋ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ



አቶ አደም ኑሪ

## “ግብር ለሀገር ክብር“ የገቢ ማስገኛ ንቅናቄ ተጨባጭ ለውጥ እያመጣ ነው”

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ያዘጋጀው “ግብር ለሀገር ክብር” በሚል እየተካሄደ የሚገኘው የገቢ ማስገኛ ንቅናቄ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እያመጣ መሆኑ ተገለፀ።

የንቅናቄው አካል የሆነ የፓናል ውይይት መድረክ ትናንት ሲካሄድ በመድረኩ የተገኙት የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ እንደገለጹት፤ የገቢ ማስገኛ ንቅናቄው መካሄድ ከጀመረ ጀምሮ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ለውጥ በማምጣት በአንድ ወር ውስጥ ለመሰብሰብ ከታቀደው ገቢ ከ1 ነጥብ 084 ቢሊዮን ብር በላይ ጭማሪ አሳይቷል፤ እንዲሁም የህግ ማስከበር እንቅስቃሴውም ጨምሯል።

የንቅናቄ ፓናል ውይይቱ “የገቢ አሰባሰብ ስኬቶች፣ ተግዳሮቶች፣ እና መውጫ መንገዶች” በሚል መነሻ ሃሳብ የተዘጋጀ ነው።

አቶ አደም ኑሪ እንደገለጹት፤ የንቅናቄ ፓናል ውይይቱ ዓላማ የገቢ አሰባሰብ ስኬቶችን በማስገንዘብ ማህበረሰቡ የሚከፍለው ግብር ለምን ዓላማ እየዋለ እንደሆነ ለማስገንዘብ ፣ተግዳሮቶችን መለየት እና መውጫ መንገዶችን ማመላከት ነው።

አቶ አደም እንደሚሉት፤ ንቅናቄው እንደ አገር የተፈጠረውን ለውጥ ማቀጣጠል፣በለውጥ ሂደት ትልቅ ሚና የሚጫወተውን ግብር ከፋይ ማነቃቃት እና በመዲናዋ ባለው ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ግብርን በታማኝነት እና በሙሉ ፍላጎት መክፈል እንዲችል ያደርጋል። የህግ ማስከበር ስራውን አጠናክሮ ለማስቀጠል ጭምርም ያለመ ነው።

አዲስ አበባ ካላት ኢኮኖሚ አንጻር የምትሰበስበው ግብር አነስተኛ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የአከፋፈል ስርዓት ማስፋት ላይ ስራዎች እንደሚቀሩ ጠቁመዋል። የንብረት ወይም የቤት ግብር ህጉ ከ1968 ጀምሮ ሥራ ላይ የነበረ እንደሆነ አስታውሰው፤ ምጣኔው ባለመሻሻሉ ምክንያት ከተማዋ ማግኘት ያለባትን ገቢ እየሰበሰበች ባለመሆኑ የንብረት ግብር አዋጅ በሚል አዋጁ ተሻሽሎ መጽደቁን ተናግረዋል። በዚህም የንብረት ዋጋን ብቻ በማሻሻል ሰፊ ግብር ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን አክለው ገልጸዋል።

የንብረት ግብር አዋጁ መኖሪያ ቤት ላይ 50 በመቶ በዚህ ዓመት እንዲተገበር፣በንግድ ቤቶች ላይ 75 ከመቶ እንዲተገበር እና በ2016ዓ.ም መቶ ፐርሰንት ተግባራዊ እንዲደረግ ውሳኔ ተላልፎ ይሄንን የማስገንዘብ ስራ እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በንቅናቄ ፓናል ውይይቱ ታክስ ከፋዩ ህብረተሰብ ግብርን በወቅቱ እንዲከፍል በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ግብአቶች ፣የመፍትሄ ሃሳቦች እና ስትራቴጂዎች እንደሚገኙበት ተገልጿል።

በመድረኩ የገቢ አሰባሰብ ስኬቶች፣ ተግዳሮቶች፣ እና መውጫ መንገዶች ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ለማ ጉዲሳ፣የኢኮኖሚ አማካሪ ዘመዴነህ ንጋቱ እና የአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ አብዱል ቃድር ሬድዋን የመነሻ ጽሁፍ አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል።

በፓናል ውይይቱ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ከአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ፣የታክስ አምባሳደሮች፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ የሚዲያ አካላት፣ ተማሪዎች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተገኝተዋል።

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ መንግስት የጣለበትን ተልዕኮና ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያስችል ተቋማዊ መዋቅር እንዲዘረጋ የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰቧል።

የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ6ኛው ዙር 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ የመንገድ አስተዳደር ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ የ2014 ክዋኔ ኦዲት መነሻ በማድረግ በትናንትናው ዕለት ውይይት አድርጓል።

የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ በውይይቱ ወቅት ሀገሪቱ ያላት ዘመናዊ የፍጥነት መንገድ ሦስት ብቻ መሆናቸውን ገልጸው፤ ነገር ግን የመንገዶቹ ግንባታ በዚህ የሚቆም አይደለም ብለዋል።

የክፍያ መንገዶች በአራቱም አቅጣጫዎች ሊገነቡ የሚችሉ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢንተርፕራይዙ አሁን ያለው መዋቅር ወደፊት ለሚገነቡት የተለያዩ ፕሮጀክቶች ብቁ መሆን ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ የተነሳው ኢንተርፕራይዙ አዳዲስ ዘመናዊ አሰራሮችን ተግባራዊ እንዲያደርግ እና ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ውጤታማ የሀብት አስተዳደር አያያዝ ስርዓት መዘርጋት እንዲችል መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ሰብሳቢዋ፤ በተጨማሪም የኮንትራት ግዢ ማዘመን እንዲችል እና ውጤታማ የፋይናንስ ምንጮችን ለማሳደግ አማራጭ የፋይናንስ ስርዓት እንዲዘረጋ ነው ብለዋል። በዚህ ላይም ትኩረት አድርጎ ሊሰራ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በተቋሙ ላይ የታየው የኦዲት ግኝት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ እስከ ሚያዝያ 25 ለቋሚ ኮሚቴው፣ ለኢንቨስትመንት ግሩፕ እና ለዋና ኦዲተር እንዲቀርብ እንዲሁም ለእያንዳንዱን የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ተደርጎ በየሁለት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርብ ቋሚ ኮሚቴው አሳስቧል።

የኦዲት ዋና መስሪያ ቤት ዋና ኦዲተር መሰረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ የተገኙባቸውን የክዋኔ ኦዲት ጉድለቶች በኋላ ለማሻሻል ያደረጉት ጥረት የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኦዲቱንም እንደ ማስተማሪያ መውሰዳቸው ሌሎች ተቋማትም ሊማሩበት የሚገባ ነው ብለዋል።







ፎቶ ገበበ ገብሬ

# ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ71 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ወደ ጎረቤት አገራት ከተላከ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ 71 ነጥብ 17 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ኃይል እየላከች ያለችው ወደ ሱዳን፣ ጂቡቲና ኬንያ ነው። በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ከኃይል ሽያጭ 89 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 71 ነጥብ 17 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ተችሏል።

ወደ ጂቡቲ ከሚላከው ኃይል 28 ነጥብ ስምንት ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 30 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር፣ ወደ ሱዳን ከሚላከው 37 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 28 ነጥብ 9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን ጠቁመው፤ ወደ ኬንያ ከሚላከው የኤሌክትክ ኃይል ሽያጭ ደግሞ 23 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 12 ነጥብ 07 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል።

በተለይ ወደ ኬንያ ከሚላከው ሀብት ለማግኘት የታሰበው ገቢ የቀነሰው ሽያጩ ከታሰበው ጊዜ ዘግይቶ በመጀመሩ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

ወደ ጂቡቲና ሱዳን ኃይል መላክ ከተጀመረ 10 ዓመታትን አስቆጥሯል ያሉት አቶ ሞገስ፤ ወደ ኬንያ ኃይል መላክ የተጀመረው ደግሞ ካለፈው ህዳር ወር ጀምሮ ነው ብለዋል።

ከእነዚህ አገራት በተጨማሪ ከሌሎችም አገራት የኃይል አቅርቦት ጥያቄና ፍላጎት መኖሩንና የመጀመሪያ ደረጃ ውይይቶች መካሄዳቸውን ያስታወሱት አቶ ሞገስ፤ ከአንዳንዶቹ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ፊርማም ተከናውኗል። ይሁን እንጂ ስምምነት ቢፈረምም ኤሌክትሪክ ለመላክ የሚያስችል መሠረተ ልማት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ሥራዎች በሂደት ላይ ይገኛሉ ።

ከደቡብ ሱዳን ጋር ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት የመግባቢያ ስምምነት የተፈረመ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ተከትሎ በባለሙያዎች ቡድን እንደ አገር ካሉን መስመሮች በየትኛው በኩል ቢኬድ ነው የሚሻለው የሚለውን፣ ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሆነ፣ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅና ሌሎችንም ሥራዎች መሥራት ስለሚያስፈልግ የኤሌክትሪክ ኃይል መላክ እንዳልተጀመረ በማሳያነት አንስተዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ሲስተዋል የነበረው የክፍያ መዘግየት አሁንም ያልተቀረፈ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሞገስ፤ ነገር ግን አሁን ላይ የሚስተዋለው ሙሉ በሙሉ ክፍያ ማቆም ሳይሆን ጊዜ ማሳለፍና ተያያዥ ክፍተቶች ናቸው። ይህም መስተካከል ስላለበት ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ፤ ወደ ውጭ የሚላከው የኤሌክትሪክ ኃይል እንደ አገር ከሚመረተው ከ10 በመቶ ያልበለጠ ነው። የሚገኘው ገቢ ግን ከተቋሙ አጠቃላይ ገቢ ወደ 30 በመቶ የሚሸፍን ነው።

በመሆኑም እንደ አገር ያለን አቅም ከፍተኛ በመሆኑ ያለንን ሀብት ከጎረቤቶቻችን ጋር ተጋርተን በጋራ ለመልማት ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑንና ወደፊት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይገኝበታል የሚል እምነት መኖሩን አመላክተዋል።

# መስማት የተሳናቸውን ዜጎች አካታች ለማድረግ አስገዳጅ ሕጎች ያስፈልጋሉ

**አመለወርቅ ከበደ**


አዲስ አበባ፡- መስማት የተሳናቸውን ዜጎች በተለያዩ ዘርፎች አካታች ለማድረግ እንደሀገር አስገዳጅ ሕጎች ያስፈልጋሉ ሲል የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ጳውሎስ ካሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መስማት የተሳናቸውን በሁሉም ዘርፍ አካታች ለማድረግ አስገዳጅ ርምጃዎች የሚጠይቁ ፖሊሲዎችና ሕጎች አስፈላጊ ናቸው።

መስማት የተሳናቸውን ዜጎች በተለያዩ ዘርፎች ላይ ተሳታፊ ከማድረግ አኳያ መሻሻሎች ቢታዩም አሁንም በርካታ ችግሮች አሉ። በትምህርት፣ በስራ ፣ በመረጃ ተደራሽነት ፣በአገልግሎት እና በመሳሰሉት የበለጠ ተሳታፊ ለማድረግ እና በሀገር ዕድገት የራሳቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የሚወጡ ህጎችና ፖሊሲዎች አስገዳጅ መሆን አለባቸው ብለዋል።

በዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብት ላይ የተቀመጠውን ስምምነት ኢትዮጵያ ፈርመው ከተቀበሉ አገራት አንዷ ብትሆንም አተገባበሩ ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

ለአብነት አንድ መስማት የተሳነው ግለሰብ በጤናው መስክ ወደሕክምና ተቋማት ለመታከም ሲሄድ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አያገኝም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤



ዶክተር ጳውሎስ ካሱ

ችግሩ በከተማና በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች ላይም ይስተዋላል ብለዋል።

መስማት የተሳናቸው ዜጎች ወደ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ቢደረግም፤ በትምህርት ቤቶች በሚዘጋጁ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮችና መሰል ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍና እራሳቸውን ለማሳደግ ዕድሉን እንደማያገኙ ጠቁመዋል።

አንድ ዩኒቨርሲቲ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ካልቀጠረ ይቀጣል የሚል ሕግ የለም።

በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው በጀት ካለው ይቀጠራል፣ ከሌለው ይተዋል። እነዚህ ነገሮች ለምን አልተደረጉም ብሎ ለመጠየቅ አስገዳጅ የሆነ ሕግ የለም ሲሉ ተናግረዋል።

በሌሎች አገራት ስራ ለመቀጠር የሚፈልግ አመልካች መስማት የተሳነው እንደሆነ ካመለከተ ድርጅቱ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አዘጋጅቶ ይጠብቃል።

ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ይሄ ዕድል የለም።

የሚወጣው ፈተና መስማት የሚችሉትን ብቻ ያማከለ ስለሚሆን ፤መስማት የተሳናቸው ስራ የማግኘት እድላቸው ጠባብ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንደገለጹት፤ በመንግስት በኩል አወንታዊ ነገሮች ቢታዩም፤ ወደታች ወርዶ ማስፈጸም የሚችል ህግ አለመኖሩ መስማት የተሳናቸውን ዜጎች ለችግር አጋልጧል።

ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ አካታችነቱ ተግባራዊነት በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ መስራት ይኖርባቸዋል ያሉት ዶክተር ጳውሎስ፤ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚወጡ ሕጎችን አካታች እንዲያደርጉ አስገዳጅ መሆን አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር እንዳስታወቀው፤ በኢትዮጵያ ከሶስት ሚሊዮን በላይ መስማት የተሳናቸው ዜጎች አሉ።

# አቶ ደመቀ መኮንን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ከታንዛኒያ ጋር ላላት ግንኙነት ትኩረት እንደምትሰጥ በመግለፅ ግንኙነቱ በኢኮኖሚው መስክ እንዲጠናከር እንደምትፈልግ ተናግረዋል።

የታንዛኒያ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳሚያ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የሁለትዮሽ ግንኙነት በተለይም በአቭዬሽንና ቱሪዝም እንዲሁም በባህል እንዲጠናከር ፍላጎቷ መሆኑን አስረድተዋል።

መንግስት የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነትን በመተግበር ሰላምን ማፅናት እንደሚፈልግ አቶ ደመቀ ተናግረዋል።

ከዓባይ ግድብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በአፍሪካ ህብረት ጥላ ስር ሁሉንም ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ በውይይት እልባት እንዲያገኝ በመጠየቅ የአረብ ሊግ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ተገቢ እንዳልሆነም ጠቅሰዋል።

በሱዳን ያለው ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደምታደርግም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር ደመቀ ተናግረዋል።

የታንዛኒያ ፕሬዚዳንት አገራቸው የኢትዮጵያ መንግሥት ሰላም ለማስፈንና ለማፅናት የሚያደርገውን ጥረት ትደግፋለች ብለዋል። የህገወጥ የሰዎች ዝውውርን በጋራ ለመከላከል ከመግባባት የተደረሰ ሲሆን፤ ታንዛኒያ ውስጥ በአዘዋዋሪዎች ተታለው በቁጥጥር ስር የሚገኙ ዜጎቻችን ተገቢው አያያዝ እንዲደረግላቸው አቶ ደመቀ ጠይቀዋል።

በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ 2,500 ዜጎቻችንን ባለፉት ወራት የመለሰ ሲሆን ቀሪዎቹም ለአገራቸው እንደሚበቁ ተገልጿል።

# ወቅቱን የዋጀና የአመራር ጥበብን የተላበሰ አመራር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደ ምክትል ርዕሰ አካዳሚዋ ገለጻ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሜሪካ ከሚገኝ ‹‹ፋውንዴሽን ፎር አንቶሎጂካል ሊደርሽፕ›› ከሚባል ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ለከፍተኛ አመራሮች ስልጠና እየሰጠ ነው።

አመራሮቹ የተለያየ ቦታ ላይ የሚሰሩ እንደመሆናቸው መጠን ከስልጠናው በኋላ በሚሰሩባቸው ተቋማት ውስጥ የአመራር ልህቀትን መለማመድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አመራሮችን እንዲፈጥሩ ማድረግ የሚያስችል ነው።

ስራዎችን በውጤታማነት መስራትና ችግሮችን የመፍታት አቅማቸው እንዲጨምር የሚያደርግም ነው።

ስልጠናው ለስድስት ቀናት የሚቆይ መሆኑን የጠቆሙት ወይዘሮ ህይወት፤ ወቅቱ አመራር ክህሎት ተላብሶ መስራት የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

በአካዳሚው የሚሰጡ ስልጠናዎች አጫጭርና የአመራር ጥበብን የሚያላብሱ መሆናቸውን በመጥቀስም ሰልጣኞች በስልጠና ያገኙትን ክህሎት በስራ ላይ ለመተግበር አላማ ይዘው እንዲሰሩ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው ብለዋል። በቀጣይም ስልጠና በወሰዱ የአመራር ተቋማት ላይ የስልጠናው ውጤት ምን እንደሚመስል ጥናት ይደረጋል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ምትኬ ሞላ እንደገለጹት፤ በስልጠናው የሲቪክ ተቋማት፣ የባንክ፣ የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተቋማት አመራሮች ተሳታፊ ሲሆኑ፤ የተሻሉ አመራሮችን ለማፍራት

ፎቶ - ዳኜ አበራ



ተጨማሪ አቅም የሚሰጥ ስልጠና ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እየተሰጠ ያለው ስልጠናም በስልጠና ልምድ ያላቸው ከአፍሪካና ከምዕራቡ ዓለም አገራት ስልጠና የመስጠት ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎችን ያሳተፈ መሆኑን ገልጸዋል።

ስልጠናው ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ለመሆን የሚያደርገውን ጉዞ የሚያግዝ መሆኑን የተናገሩት ፕሮፌሰሯ፤ መምህር የነበረ ዲን፣ ዳይሬክተር ይሆናል፤ ይህ ማለት አመራር ሲሆን የአስተዳደር ስልጠና ወስዷል ማለት አይደለም።

ይህን ክፍተት ለመሙላት የሚሰጠው ስልጠናም የአመራር ሚና እንዴት ውጤታማ እንደሚሆን መንገድ የሚያሳይ ነው ብለዋል።

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዴት ውጤታማ እንደሚሆን ጥበብ የሚያላብስ ስልጠና በመሆኑ አስፈላጊ ነው። ወቅቱ ልህቀትን የተላበሰ አመራር የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ክፍተቱን በማየት መሙላት ወሳኝ ነው። ለዚህም ስልጠናው ትልቅ አቅም ይፈጥራል። በአመራርነት ዘመን ሁልጊዜም የተሻለ መንገድ አለ።

የተሻለውን መንገድ ለመፈለግ ስልጠናው ወሳኝ መሆኑን አብራርተዋል።

የስልጠናው ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት፤ ስልጠናው ትክክለኛ የአመራር ክህሎትን ለማሳደግ፣ የአመራር ጥበብን ለማጎልበትና ክፍተቶችን ለመሙላት ሚናው የጎላ ነው ብለዋል።

# ኢፕድ እና ኢቢሲ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በአንጋፋ ተቋማቱ መካከል በትብብር ለመስራት የተደረሰው ስምምነት ለሌሎች የሚዲያ ተቋማትም ትምህርት የሚሰጥ ነው ሲሉ ወይዘሮ ሔለን ተናግረዋል።

ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ እንደገለጹት፤ ኢፕድ በሕትመት የሚዲያ ዘርፍ በአፍሪካ አህጉር ደረጃ ቀደምት ከሆኑ ተቋማት መካከል አንዱ ነው፤ ኢቢሲም በብሮድካስት ሚዲያው የረጅም ዓመት ልምድ አለው።

በመሆኑም የሀገርን ታሪክ ሰንደው የያዙት ሁለቱ ተቋማት በጋራ የሚሰሩባቸውን መንገዶች ማስፋታቸው ጠቃሚ ነው። በየተቋማቱ ያሉትን ታሪኮች ሰንዶ መያዝ ብቻ ሳይሆን ለትውልዱም ማሳየት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ኢፕድና ኢቢሲ በጋራ በመስራታቸው ለሀገር ያላቸውን አበርክቶ ያሳድገዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብዱራህማን ሩቤ በበኩላቸው፤ ተቋማቱ ቀድሞም በጋራ ሲሠሩ ነበር። አሁን ላይ ትብብራቸውን የሚያጠናክር ስምምነት አድርገዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢፕድና ኢቢሲ አንድ ላይ መሥራት የጀመሩት ዛሬ አይደለም። ኢፕድ ስለኢትዮጵያ የተሰኘውን መድረክ ሲያዘጋጅ ኢቢሲ አብሮ ነበር። ዜናዎች ሲሰሩ ኢቢሲ የኢፕድን ኢፕድ የኢቢሲን ዜና ስናስተላልፍ ነበር ያሉት አቶ አብዱራህማን፤ በቀጣይም የጋራ አቅማችንን በመጠቀም ውጤታማ ሥራዎችን በጋራ እናከናውናለን ብለዋል።

እንደሚዲያ ስንደመር ጠንካራ ሀገራዊ ተቋማትን እንገነባለን ያሉት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ኢፕድና ኢቢሲ በጋራ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራዎችን ለማከናወን ስምምነት ላይ በመድረሳቸው ደስተኞች ነን ሲሉ ገልጸዋል።

ስምምነቱ ኢፕድና ኢቢሲ ፕሮግራሞቻቸውን በጋራ ለማስተዋወቅ፣ የተለያዩ ሁነቶችን በጋራ ለማዘጋጀትና በተለያዩ ሥራዎች ላይ በትብብር ለመሥራት እንደሚረዳ ተገልጿል።

ተቋማቱ የተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ በሕትመት ኢንዱስትሪና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው ዘርፍ ያላቸውን ተሞክሮ እንዲጋሩ እና ትላልቅ ሀገራዊ ሥራዎችን በቅንጅት እንዲሠሩ እንደሚያስችል ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሕትመት ዘርፍ ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ እየሰራ የሚገኝ የሚዲያ ተቋም ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ደግሞ ከ1923 ዓ.ም ጀምሮ እየሰራ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው።

# ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከወጪ ንግድ ሁለት ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረመስቀል ጫላ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው ከተጠሪ ተቋማቱ እና ከክልል ንግድ ቢሮ ኃላፊዎች ጋር የ9 ወር የስራ አፈፃፀም ሲገመግም እንደገለጹት፤ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከወጪ ንግድ ሦስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት አቅዶ ሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል።

ይህ አፈፃፀምም ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ312 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል።

ለወጪ ንግድ ገቢው ግብርና 77 በመቶ፤ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ 11 በመቶ፣ ማዕድን ስድስት ነጥብ አምስት በመቶ ፣ ኤሌክትሪክና ሌሎች ምርቶች ሶስት ነጥብ ሶስት በመቶ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

ለገቢው ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ቅናሽ ያሳየውም የዓለም ገበያ መቀዛቀዝ ፣የኮንትሮባንድ ንግድና የፀጥታ ችግሮች ምክንያት መሆኑን አመልክተዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈፃፀም ባለው ሂደት የተቀናጀና በተናበበ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ነው የተናገሩት።

በቀሩት ሁለት ወራትም ክፍተቶችን አርሞ አፈፃፀምን ወደላቀ የስኬት ደረጃ ለማድረስ የማያቋርጥ ርብርብ ማድረግን ይጠይቀናል ብለዋል። ክልሎች ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን ሀገራዊ የንግድ ስርዓት ለማዘመንና የሀገር ውስጥ ህገወጥ ንግድን ለመቆጣጠርና ለችግሮች የጋራ መፍትሔ ለመፈለግ በጋራ እየሰሩ ነው ብለዋል።

የኑሮ ውድነትን ለማረገብም መንግስት መሰረታዊ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ 10 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ሸማቹን የደጎመ መሆኑን ገልፀዋል።

በዘላቂነት የምግብ አቅርቦቱንና ፍላጎቱን ለማጣጣምም የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ መንግስት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም ለማዳበሪያ ብቻ ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ ድጎማ በማድረግ ለአርሶ አደሩ እያቀረበ ነው ብለዋል።

መንግስት ዘይት፣ በውጭ ምንዛሪ ግዢ በማቅረብ እና ምርት ያቆሙ የስኳር ፋብሪካዎችን ወደ ምርት በማስገባት ገበያውን ለማረጋጋት ጥረት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል። በህብት ስራ ማህበራት በኩልም ጤፍ፣ ስንዴና መሰል የግብርና ምርቶች ለሸማቹ እየቀረቡ መሆኑን ገልጸዋል።

አምና 260 ብቻ የነበሩ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችን ዘንድሮ ወደ 500 ማሳደግ መቻሉንም ገልፀዋል። በቀጣይም በመላ አገሪቱ በማስፋፋት አምራቹና ሸማቹ በቀጥታ የግብርናና የፋብሪካ ምርቶችን እንዲገበያይ በትኩረት እንደሚሰራ አመልክተዋል።

በቀጣይም የዋጋ ንረት፣ ህገወጥ ንግድ፣ ምርትን ሆን ብሎ ለገበያ ያለማቅረብና የኮንትሮባንድ መስፋፋት ችግሮች ለመፍታትም ከክልሎች ጋር በቅንጅት በመስራት ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራባቸው ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፍቅር፣ ሰላምና ወዳጅነት የኢትዮጵያውያን ውድ እሴቶች ናቸው!

ነገርን ከስሩ፣ ውሃን ከጥሩ፣ እንዲሉ አበው፤ መወደዳችን፣ ሰላምና ይቅርታችን፣ ትብብርና ኅብረታችን፣ ፍቅርና ወንድማማችነታችን ሁሌም ውድ የሆኑ ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችን ናቸው። ከእውነት የሆነ እውነት ነውና አይሸረሸርም፤ ከልብ የሆነም ስር ሰዷል እና አይነቀልም። እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ብዙ ነገሮቻችን ከልብ ጋር ቁርኝት እንዳላቸው በንግግሮቻችን ሳይቀር ስንገልጽ እንሰማለን። ሲናገሩ - ከልቤ ነው፤ ሲያዳምጡ - ከልብ አድምጡ፤ ሲወዱ - ከልቤ ገባ፤ ሲጠሉ - ከልቤ ወጣ፤ ሲያዝኑ - ልቤን ሰበረው፤... ማለታችን የተለመደ ነውና።

ኢትዮጵያውያን፣ አገራቸውን ከልብ ይወዳሉ፤ በሃገራቸው ክብርና ሉዓላዊነት የመጣባቸውን ከልብ ይዋጋሉ፤ ስለ ሕልውናቸው የተገዳደራቸውን ከልብ ያወግዛሉ፣ ታግለውም አደብ ያስይዛሉ። በአንጻሩ በፍቅር የቀረባቸውን በልባዊ ፍቅር ይቀበላሉ፤ በችግራቸው ጊዜ የደረሰላቸውን ከልብ ያከብራሉ፤ የደገፋቸውን ከልባቸው ይደግፋሉ፤ በድሎ ለይቅርታ እጁን የዘረጋም ሲኖር ከአንገት ሳይሆን ከልብ ይቅር ማለትን ያውቃሉ።

ይሄን ድንበር አቋርጦ አገር የደፈረን ወራሪ ጠላት ሳይቀር ድባቅ በመቱ ማግስት ስለ ጥፋቱ የበለጠ ከመቅጣት ይልቅ ይቅርታቸውን ከልብ ሰጥተው ወዳጅነትን መሥርተው ሲኖሩ መታየታቸውም ለዚህ ነው። ይሄ ደግሞ በወንድማማቾች መካከል ሲሆን ደግሞ ወንድም ወንድሙን ሲበድል ይቅር ማለትም ኢትዮጵያዊ እሴትም፣ ሃይማኖታዊ ትዕዛዝም ጭምር እንደመሆኑ ስሜቱ ከፍ ይላል።

በዚህ የወንድማማችነት ውስጥ በሚፈጠር ይቅርታ እና በፍቅር መልክ መገለጥ ምክንያትም በዘመናት መካከል የሚፈጠሩ መቃቃሮች በይቅርታ ታልፈው ኢትዮጵያውያን በአንድ ቆመው ጠላትን ሲመክቱ ታይተዋል። ቂምና ቁርሾን ሽረው ችግር በገጠማቸው ጊዜ አንዳቸው ለአንዳቸው አለኝታና መከታ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ስለ ሃገራቸው ሉዓላዊነት፣ ስለ ራሳቸው ክብርና ደህንነት ሲሉም ከውስጥም ከውጪም የሚነሱ የጥፋት ቡድኖችን አደብ ለማስያዝ በጋራ ተዋድቀው፤ በጋራ አገር አጽንተው በትውልድ ቅብብሎሽ ለዚህ በቅተዋል።

ዓለማችን የሁለት ተቃርኖዎች ስሪት እንደመሆኗ፤ በሰው ልጆች የኑሮ ሂደትም እነዚህ ሁለት ተቃርኖዎች መፈራረቃቸው አይቀሬ ነው። ይሁን እንጂ ጨለማ በብርሃን እንደሚሸነፍ ሁሉ፤ ጥላቻ በፍቅር፣ ፅብም በይቅርታ መሸነፋቸው አይቀሬ ነው። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ላለፉት ሦስት ዓመታት የገጠማቸውም ይሄው ነው።

አለመግባባት ወደ ግጭት፣ ግጭት ወደ ጦርነት አድጎ አያሌ ዜጎች አካላቸውን፣ ሕይወታቸውን፣ ሃብት ንብረታቸውን አጥተዋል። ሃገርም በዚሁ ጦርነት አንድም ውድ የሆኑ ዜጎቿን፣ሁለተኛም ኢኮኖሚዋን ተነጥቃለች። በጥቅሉ በወንድማማቾች መካከል የተደረገው ጦርነት ከፍ ያለ ማኅበራዊ፣ ሥነልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብሎም ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጠባሳዎችን አሳርፎ አልፏል።

ይሄ ክፉ ገጽ ታዲያ ጠይሞ አልቀረም፤ ኢትዮጵያውያን ለሃገራቸው ሉዓላዊነት እና ለራሳቸውም ደህንነት ሲሉ ከልባቸው ተዋግተው ሕልውናቸውን እንዳስቀጠሉ ሁሉ፤ አገር የሚጸናው፣ ደህንነትም በዘላቂነት የሚረጋገጠው በጦርነት ሳይሆን ፍቅር ውስጥ በሚገኝ ሰላም መሆኑን ያምናሉና፤ ስለ ሰላም ዘምረው ሰላማቸውን ለማጽናት ቁጭ ብለው መከሩ። በምክራቸውም መሠረት የጦር ነፍጣቸውን ጥለው የሰላም ርግብን አነሱ። እናም ኢትዮጵያውያን ከግጭታቸው ማግስት በይቅርታ ልብ ተገናኝተው በፍቅር ተቃቀፉ። ይሄ ይቅርታና የሰላም መንገድ ጠላቶችን ቢያበሳጭም፤ ወዳጆችን አስፈንድቋል፤ ኢትዮጵያውያን ዳግም በኅብር ደምቀው እንዲገለጡ አድርጓል።

ኢትዮጵያም ስለ ሰላሟ የተጉላትን በአደባባይ አመሰገነች፤ ለሌሎች አርዓያነታቸውን ገለጠች። ከዚህም በላይ ልጆቿ ይሄን የሰላም ጅምር፣ የይቅርታ መንገድ፣ የፍቅር መድረክ ከፍ ወዳለ ምዕራፍ እንዲያሸጋግሩ የአደራ ቃሏን አስተላለፈች። በጠቅላይ ሚኒስትሯ አማካኝነትም፤ ለሕልውናዬ ስትሉ ከልባችሁ ተዋግታችሁ ከፍ እንዳደረጋችሁኝ ሁሉ፤ ቀጣይ የሚኖራችሁ አብሮነት ያማረና የሰመረ እንዲሆን ይቅርታችሁም ከልብ ይሁን አለች።

የይቅርታው መንገድ ሰምሮ በፍቅር ሊጸና፤ የሰላሙ ሰገነትም ጸንቶ ሊገለጥ ይገባዋልና የይቅርታችሁ ቦታ ከልባችሁ ይሁን፤ በሰላም ትግላችሁም ከፍ ያለው ጀግንነታችሁ ይገለጥበት፤ ወንድማማችነታችሁ እንደትናንቱ ደምቆ ይታይልኝ አለች። በመሆኑም የእናት ቃል ሊከበር፤ የወንድማማቾችም ይቅርታ ከልብ ሰርጾ የታለመውን ሰላም ያጸና ዘንድ የተገባ ነው። ስለሆነም ሁሉም ዜጋ ይቅርታውን ከልቡ፤ ሰላሙንም ከደጁ ሊያደርግ ያስፈልጋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የመረዳዳትና የመተጋገዝ እሴቶቻችን እንዲዳብሩ

ትንሳኤ አበራ

የሰው ልጆች ሕይወት በፈተና የታጀበ እንደመሆኑ መጠን በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል። ኑሮ በአንድ በኩል ሲሞላ፤ በሌላ በኩል እየጎደለ ቀዳዳው እየበዛ ማግኘትና ማጣት እየተፈራረቁ የሚቀጥል ሂደት ነው።

በዚህ ረጅም የሕይወት ሰንሰለት ውስጥ ለማለፍ ደግሞ አንዱ ሲደክም፤ ሌላውን እየደገፈ በመረዳዳትና በመተጋገዝ ሕይወትን ለማስቀጠል በአብሮነት መጓዝ የግድ ይላል። መረዳዳትና መተጋገዝ ደግሞ መልካምነት ብቻ አብዝተው የሚጠይቁ የበጎነት ተምሳሌት ናቸው።

በተለይ ኢትዮጵያውያን ዘንድ መረዳዳትና መተጋገዝ የማንነታችን መለያ የሆኑት እሴቶቻችን ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖት፣ብሔርና ቋንቋ ሳይመርጥ ሁሉም በአንድ ዓይን እየተመለከተ ያለው ፤ የሌለውን እየደገፈ በመስጠትና በመቀበል ውስጥ በአብሮነት እጅ ለእጅ ተያይዞ ረጅም ዓመታት የኖረ ሕዝብ ነው ።

እነዚህ ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችን ከማኅበረሰቡ ጋር አብረው የኖሩ ጎልተው የሚታዩ የሁል ጊዜ ተግባራት ናቸው። በበዓላት ወቅት ደግሞ ከሌላው ጊዜያት ለየት ባለመልኩ ይከወናሉ። ኢትዮጵያውያን በተለይ ለበዓላት የሚሰጡት ቦታ ትልቅ በመሆኑ በበዓል ወቅት ዘመድ ከአዝማዱ ፣ጓደኛ ከጎረቤት ሁሉም በአንድነት ተሰብስቦ የሚገናኝበትና በዓል በጋራ የሚያከብሩበት እንደመሆኑ መጠን ዘመድ አዝማድ፣ ጠያቂና ደጋፊ የሌላቸው፣እጅ ያጠራቸውን ሰዎች መጎብኘት የተለመደ ነው።

የወደቁትን ማንሳት፣ የደከሙትን መደገፍ ሰው በመሆናቸው ብቻ የምናደርገው የሰብዓዊነት ተግባር መሆኑን ሁሉም ሃይማኖቶች ሲደግፉትና ሲያስተምሩ የኖሩት አስተምሮት ነው።

ከሃይማኖታዊ አስተምህሮቶቻችን ባሻገርም መረዳዳትና መደጋገፍ ባሕል ሆኖ እንዲቀጥል አበው «መስጠት ለራስ ነው፤ መልሶ ይከፍላል» እያሉ በሰዎች መካከል መረዳዳትና መደጋገፍ አስፈላጊ መሆናቸው ሲያስተምሩን ኖረዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም ባለው አቅም እርስ በእርስ እየተሳሰበ፣እየተደጋገፈና እየተረዳዳ የመኖር ባሕልን ያዳበረ ነው።

ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያዊ ትስስሮቻችና አብሮነታችን የተጋመዱት በተግባር በምንኖራቸው እሴቶቻችንን ነው። በተግባር የሚገለጹት እሴቶቻችን ያለው የሌለውን በመርዳትና በመደጋገፍ እጅ ለእጅ ተያይዘው በአብሮነትና በአንድነት በመጓዝ እስካሁን ሊያዘልቁ ችለዋል።

በዚሁ ሳምንት በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት የተከበረው የኢድ -አልፈጥር በዓል በተለየ መልኩ ሁሉንም ባሳተፈ ሁኔታ መረዳዳቱና መደጋገፉ የሚጠናከርበት ጊዜ ነው።

የኢድ-አልፈጥር በዓል የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ቤት ያፈራው በጋራ ተቋደሶ እርስ በእርስ በመረዳዳትና በመደጋገፍ የሚያሳልፉበት ነው። አስታዋሽ ያጣን ወገን በማስታወስ ያለው ካለው ላይ ፤ የሌለውም ደግሞ ከዚያው ላይ ቀንሶ በመስጠት የወገን አለኝታነቱን የሚያስመሰክርበት ነው።

በተለይ በኢድ -አልፈጥር በዓል መረዳዳትና መደጋገፉ በብዙዎች ዘንድ የሚታይና የሚዘወተር ነው። ይህ በብዙዎች ዘንድ በጉጉትና በናፍቆት የሚጠበቅ በዓል የበርካቶች እጅ ሰደቃ(ምፅዋት) ለመስጠት በሰፊው የሚዘረጋበት በመሆኑ በርካታ ድጋፍ የሚሹ ወገኖች በሚደረግላቸውም ድጋፍ የወገናቸውን የአብሮነት የሚያዩበት በጋራ ማዕድ የሚቋደሱበት የእርስ በእርስ ቁርኝነት የሚጠናከርበት ወቅት ነው።

በምንም ጊዜ ቢሆን መስጠትም ሆነ በመቀበል አዲስ ባይሆንም ከሌላው ጊዜ በተለይ መልኩ በአፅዋማትና በበዓላት ወቅት የሚመፀውቱ (የሚሰጡ) ሰዎች እጆች እጅግ በዝተው ይታያሉ። ሆኖም ግን የበጎነት ተግባር በአፅዋማትና በበዓላት ወቅት ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግን ይገባል ።

በተለይ በሀገራችን በርካታ ድጋፍ የሚሹ ሰዎች ባሉበት በዚህ ወቅት አበው «ያለውን የሰጠ፤ ንፉግ አይባልም» እንደሚሉት በአካባቢያችን ፣ በየጎረቤታችንን ያሉ እጅ ያጠራቸውን ፣ ድጋፍ የሚሹ ሰዎች መጎብኘት ሰብዓዊ ግዴታችን ነው ።

ሰውን ለመርዳትም ሆነ ለመደገፍ የሚያስፈልገው ሰው መሆን ብቻ በመሆኑ አጠገቡ ያለ ድጋፍ የሚያስፈልገውን ወገናችን በመመልከት በተቻለ አቅም ከተረዳዳን ችግርን ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ ባይቻልም ማቅለል እንችላለን።

«ሰውን መርዳት ደስ ይለኛል፤ነገር ግን ምን አለኝና ምኔን ልስጥ፣ ምን ልደግፍ --- »የሚሉ ሰዎች በርካታ ናቸው ፤ ሰውን መርዳትና መደገፍ (መስጠት) ምንም አይነት መስፈርት ሳይስፈልገው ሰው የሆነ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ሊያከናወነው የሚችለው በጎ ተግባር መሆኑን የሥነልቦና ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ባለሙያዎቹ እንደሚሉት፤ ሰውን ለመርዳት ሲያሰቡ አሁን ምን አለኝና ሲኖረን ነው መስጠት ያለብን ብለን የሚያሰቡ ሰዎች አስተሳሰባቸው ትክክል አይደለም። መስጠትና መቀበል ተፈጥሯዊ ክስተቶች እንደመሆናቸው መጠን በመስጠት ሰውን መርዳት መቻል ደግሞ ከሁሉም በላይ ጠቀሜታ ለሰጪው ሰው ነው። ሰውን የሚረዳ ሰው ሰውን በመርዳቱ ብቻ ውስጡ የሚፈጥረው ደስታ ከሁሉ በላይ ነው።

መስጠት ሆነ መቀበል ውስጥ በሰጪውም ሆነ በተቀባይ ዘንድ የሚፈጠሩት የደስታ ስሜት ቀላል የሚባል አይደለም። በሚሰጡም ሆነ በሚቀበሉ ሰዎች ዘንድ ያለው ታላቅ ስሜት ሌሎች ሰዎች ላይ እንዲጋባባቸውና እንዲረዱ በማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ መስጠት እየፈለጎ እኔስ ምንአለኝና ምኔን ልስጥ ነው የሚሉ ሰዎች በቂ ትምህርት የሚያገኙበት ይመስለኛል።

ሰው ሆነው መስጠት የማይችሉ ነገር እንደሌላ በመረዳት መስጠት በገንዘብና ቁሳቁስ ከመለካት ባሻገር በጥልቀት ማየት ያስፈልጋል። ፍቅር በመስጠት፣ትንሽ ጊዜን አብሮ በማሳለፍ እና በተለያዩ ተነግረው የማያልቁ በጎ ምግባራት በመኖራቸውን ሰዎች መርዳት እንደሚቻል ትምህርት ሊያገኙ ይገባል ።

እነዚህ ለሌሎች አርአያ ሊሆን የሚችል የመረዳዳትና የመተጋገዝ እሴቶቻችንን እንዲህ በበዓላት ወቅት ፍንትው ብለው እንደሚታዩ ሁሉ እንዲሁ እንደአማረባቸው እንዲቀጥሉ ማድረግ ይገባል። በተለይ በተለያየ ምክንያት ድጋፍ የሚሹ ወገኖቻችን በበዙበት በዚህ ወቅት አለንላችሁ ማለት ከሁላችንም ይጠበቃል።

በኢትዮጵያ ለመብላት ከተዘጋጀው ምግብ 30 በመቶ የሚበላ ሲሆን 70 በመቶው የሚጣል እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከዚህ ውስጥ ከሚበላው ይልቅ የሚጣለው በልጦ ይታያል። ታዲያ የአኗኗር ዘይቤያችንን በመቀየር በአግባብ መጠቀም ከቻልን አይደለም ለወገን ለሌላውም መትረፍ እንችላለን ባይ ነኝ።

ለወገን ደራሽ ወገን ነው እንደሚባለው ሌላ የውጪ አካል መጥቶ እንዲረዳን አንጠብቅምና እኛው ለእኛ አለኝታ መሆን አለብን። ምንም የሌላቸው ድጋፍ የሚፈልጉ ወገናችን ከጎናችን ቁጭ በላ መብላት የሚያስችል ሥነልቦና የለንምና መረዳዳትን ባህላችን አድርገን ልናስቀጥል ይገባል። ኢትዮጵያዊ የመረዳዳትና የመተጋገዝ እሴቶቻችን እንዲያብቡ ሁላችንም የበኩላችን ኃላፊነት መውጣት አለብን። በኢድ-አልፈጥር።

# ነፃ ሀሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# መኃልየ-መኃልይ ዘ ሰላም ጀግና ፤

መኃልየ-መኃልይ ዘሰሎሞን ከሁሉም የሚበልጥ የሰለሞን መዝሙር ማለት መሆኑን በዚህ ዓምድ ደጋግሜ የገለጽሁ ቢሆንም ዛሬም የመጣጥፌ ርዕስ ማድረግን ስለመረጥሁት ለማስታወስ እወዳለሁ። የሁለት ፍቅረኛዎች ንግግር ተደርጎም ይወሰዳል። የፍቅረኞች ንግግር በግጥም ነውና ምት፣ዜማ አለው። ሰለሞን ስለ ሙሽራውና ሙሽሪት ፣ ስለፈጣሪና ስለ ቤተ ክርስቲያን የዘመራቸውን 1ሺህ 5 መዝሙሮችን ይመለከታል። ሙሽራው ልዑል እግዚአብሔርን ሲወክል ሙሽራይቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት።

መኃልየ እንደ ለዘብና ወረብ አይነት በፍጥነት የሚዘመር ጥዑም መዝሙር ነው። መዝሙሮቹ በተለያየ ስልት ዜማ ቢደጋገሙም ያው ስለፈጣሪና ቤተ ክርስቲያን ክብር ፣ ቅድስና የሚመሰክሩ ናቸው። ይህ መጣጥፍ ዛሬ ለምንገኝበት አንጻራዊ ሰላም ዋጋ የከፈሉ ግለሰቦችንና ተቋማትን የሚዘክር፣ የሚያወድስና የሚያከበር ሆኖ ስለአገኘሁት፤" መኃልየ-መኃልይ ዘ ሰላም ጀግና "ማለትን መርጫለሁ።

ለተደረሰው የሰላም ስምምነት እርሾና መሰረት ሆኖ ያገለገለውና ዛሬ ላይ ፍሬ ለማፍራቱ ዋናው ምክንያት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰላምን ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት መሻታቸው ነው፤ ይሄንን ደግሞ በፕሪቶርያው ስምምነትም ሆነ ከዚያ በኋላ በነበረው የትግበራ ምዕራፍ በቁርጠኝነት በመተግበር አረጋግጠዋል። ስለሆነም ዛሬ ለምንገኝበት አንጻራዊ ሰላም ያበቁንን ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ጥምር ኃይሉን "መኃልየ-መኃልይ ዘ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ጥምር ኃይሉ፤"ብያለሁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅድመ ጦርነቱ፣ በጦርነቱም ሆነ በድኅረ ጦርነቱ ለሰላም ያላቸው ቁርጠኝነት ተከታታይነትና ወጥነት ያለው መሆኑ፤ ከአንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ በተግባር አረጋግጠዋል። ከዚህም ባለፈ ለሰላም የሄዱበት ርቀት፤ ጦርነት የመንግሥታቸው ፍላጎት እንዳልሆነና ፍላጎታቸው ልማትና ብልጽግና እንደሆነ መወትወታቸው፤ መንግሥታቸው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደራደር ዝግጁ መሆኑን መግለጻቸው፤ ሕወሓት ለሰላም እድል ፈንታ እንዲሰጥ አድርጎታል። ለሰላም ያላቸው ፍላጎት በአፍሪካ ኅብረት ፣ በምዕራባውያንና በዓለምአቀፉ ማኅበረሰብና ተቋማት ዘንድ ሳይቀር እውቅና ማግኘቱ ሌላው ምክንያት ነበር።

እንደ የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ድርድር፤ "ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ" የሚል ዘመኑንና ትውልዱን የዋጀ መርሕ የኅብረቱን ተቋማት ያነቃቃና እውቅና የሰጠ ታሪካዊ አጋጣሚ ሲሆን፤ ኅብረቱንም የድርድሩ አስኳል እንዲሆን አደፋፍሮታል። የምዕራባውያን ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነትን ማስቀረት ከመቻሉ ባሻገር ምዕራባውያን ሳይወዱ ይሄን መርሕ እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል።

ምዕራባውያን የመንግሥትን የሰላም ቁርጠኝነት ለመቀበል ጊዜ ቢወስድባቸውም ፤ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሙሳ ፋቂ መሐመት በወቅቱ መንግሥት ጦርነቱን በሰላም ድርድር ለመቋጨት ያሳየው ቁርጠኝነት ይበል የሚያሰኝ ነው በማለት የምዕራባውያንን በስጋት ላይ ያነጣጠረ የስጋት ደመና ገፈዋል። የአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ የሆኑት የቀድሞው የናይጄሪያ

> **ለተደረሰው የሰላም ስምምነት እርሾና መሰረት ሆኖ ያገለገለውና ዛሬ ላይ ፍሬ ለማፍራቱ ዋናው ምክንያት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰላምን ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት መሻታቸው ነው፤ ይሄንን ደግሞ በፕሪቶርያው ስምምነትም ሆነ ከዚያ በኋላ በነበረው የትግበራ ምዕራፍ በቁርጠኝነት በመተግበር አረጋግጠዋል**

ፕሬዚዳንት ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "የጠየቅኩትን ትኩረት ሰጥተውኛል። በሚገባው ልክ አስተናግደውኛል። አደራዳሪነቴን ተቀብለውኛል። "ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሰላም ያላቸውን ቁርጠኝነት መስክረዋል። ወደ አደራዳሪዎች ስንመለስ ደግሞ በተለይ የቀድሞው የናይጀሪያ ፕሬዚዳንት ኦባሳንጆ በታሪክ ድርሳናችን በወርቃማ ብዕር ተጽፎ ሲዘከር ይኖራል።

የአደራዳሪዎች ሚናም በቅጡ እውቅና ሊቸረው ይገባል። የአፍሪካ ኅብረት "ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ" የሚለውን መርሕ አበክሮ በመቀበል የሰላም ድርድሩን በመምራትና በማሳለጥ የአንበሳውን ድርሻ ቢጫወትም የቀድሞው የናይጀሪያ ፕሬዚዳንት ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ ተደጋጋሚ ጥረት ግን ከፍ ያለ ነው። በዚህ እድሜያቸው በማይመች ሁኔታ በተደጋጋሚ ወደ አዲስ አበባና መቀሌ በመመላለስ ስምምነቱ እውን እንዲሆን ያበረከቱት አስተዋፅዖ ምንጊዜም ሀገራችን አትረሳውም።

ከ10 ተከታታይ ቀናት እልህ አስጨራሽ ጥረት በኋላ ፕሪቶሪያ ላይ የሰላም ስምምነቱ ሲፈረም ኦሉሴጎን የተፈጠረባቸው ስሜት በራሱ ብዙ ይናገራል። የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬኒያታና የደቡብ አፍሪካ የቀድሞዋ ፕሬዚዳንት ፉምዚል ማምቦ ንጉካ አበርክቶም በልኩ እውቅና ሊቸረው ይገባል።"መኃልየ-መኃልይ ዘ አባሳንጆ" ብያለሁ።

ከሁሉም በላይ ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ የሚለው መርሕ አፍሪካውያን ያለማንም ጣልቃ ገብነት ችግሮቻቸውን መፍታት እንደሚችሉ ከማረጋገጡ ባሻገር በትልቅ የእንችላለን መንፈስ የተመራ የሰላም ፍኖተ ካርታ ነው።

በትግራይ ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች የደረሰው ውድመት ከብዙ መቶ ቢሊዮኖች በላይ የሚገመት ነው ማለት ይቻላል። መቶ ሺዎችንም ለሞት ፤ ከቤት ንብረታቸው ያፈናቀለ ነው። የሰላም ስምምነቱ እንግዲህ ይሄን አውዳሚና ዘግናኝ ጦርነት ነው ያስቆመው።"መኃልየ ዘ አፍሪካ ኅብረት"ብያለሁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት አስመልክቶ በወቅቱ በአርባ ምንጭ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ላይ እያሉ ባስተላለፉት መልዕክት፤"... አሁንም ለሰላም ላባችንን ብናፈስ፣ በጦርነት የወደሙብንን አካባቢዎች መልሶ ለመገንባት ካለን ላይ ብናዋጣ እናተርፋለን እንጂ አንጎዳም። በሙሉ ልብ ትግራይንና የትግራይን ሕዝብ ለመገንባት ወደቀደመው የሀገር ስሜት ለመመለስ አብረን እንድንቆም በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ፤ ..." ብለዋል። የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ ማለትም ከሰሜን ዕዝ ጥቃት በኋላ ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት ትግራይን ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠረበትና ጊዜያዊ አስተዳደር በተቋቋመበት ለክልሉ መልሶ ማቋቋም ቀድመው የደረሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ነበሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ከመጽሐፋቸው ሽያጭ 200 ሺ ብር ከአንድ ወር ደመወዛቸው ጋር እንዲሁም ሦስት ቦቴ መኪናዎችን ለንጹሕ መጠጥ ውሃ ማመላለሻ ለግሰዋል። የፌዴራሉ መንግሥት ደግሞ ለመልሶ ግንባታ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጓል። የኦሮሚያ፣ የጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 282 ሚሊዮን ብር መቐሌ በመገኘት በመለገስ አለኝታነታቸውን አረጋግጠዋል።

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር በተለይ ለትምህርት ዘርፉ መልሶ ግንባታ 320 ሚሊዮን ብር በጀት አዞሮ እየሠራ ነበር። ከዚያ በፊት የአፋርና ሌሎች ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የተለያዩ ተቋማት ለትግራይ ሕዝብ የገንዘብና የተለያዩ የዕለት ደራሽ ድጋፎችን አድርገዋል።

የፌዴራል መንግስት ከ4 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ወገኖች እርዳታ ያቀረበ ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችም የጨኸታቸውን ያህል ባይሆንም መጠነኛ ድጋፍ ማድረጋቸው አይረሳም። ይህ አኩሪ የተቀናጀ ርብርብ ዜጎችን ከረሀብና ከጠኔ ከመታደጉ ባሻገር የትግራይ ሕዝብ በክፉ ቀኑ የሚደርስለት አለኝታ መንግሥትና ወገን እንዳለው ያረጋገጠ ነበር። ዕጣ ፈንታውና መጻዒ እድሉ ከኢትዮጵያ ጋር መሆኑንም ያስመሰከረ ሠናይ ተግባር ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ መሪነት ከመጡበት ሰዓት አንስቶ በትግራይ ክልል ይህ ቀውስ እንዳይቀሰቀስ ትሕነግን ለማግባባት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ያላደረጉት ጥረት የለም። እውነት ለመናገር የሰላምን ውድ ዋጋ እንደ እሳቸው አበክሮ የተረዳ አልነበረም። ከበዓለ ሲመታቸው የፓርላማ የመጀመሪያ ንግግር እስከ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም።

ለሰላም ካላቸው ቁርጠኝነትና ጦርነት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ በውትድርና ሕይወታቸው ጠንቅቀው ስለሚያውቁት፤ ጓደኞቻቸውንና ወንድማቸውን ስለነጠቃቸው፤ ጦርነት የሀገርን ኢኮኖሚ ምን ያህል እምሽክ ድቅቅ እንደሚያደርግና እንደሚያወድም አበክረው ስለተገነዘቡና የ117 ሚሊዮን ሕዝብ መጻኢ እድልን እንደሚወስን በመረዳታቸው፤የትግራይ ሕዝብም ጦርነት ይበቃዋል በሚል እምነት እንዲሁም ለትግራይም ሆነ ለሌሎች ሕዝቦች ደህንነት ሲሉ እስከ መጨረሻው ሰዓት ሆደ ሰፊነትንና ትዕግስትን መርጠዋል።

ሀገሪቱን ከጠብመንጃ አዙሪት ለማውጣትና ከዚህ ቀደም የነበሩ ገዥዎች ያልሄዱበትን የሆደ ሰፊነትና ቁጭ ብሎ የመነጋገር መንገድ በመምረጣቸው በልኩ እውቅና ሊሰጣቸውና አብዛኛው ዜጋ ከጎናቸው ሊቆም ሲገባ መንግሥታቸው በልፍስፍስነት ከመወቀሱ ባሻገር ፓርቲያቸውም ሆነ እሳቸው ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ደጋፊያቸውና ተከታያቸው ብዥታና ድንጋሬ ላይ እንዲወድቁ አድርጓል።

ሰከን ብሎ ለተረዳው ግን ለሰላም ያላቸው ቁርጠኝነት የሀገራችንን ፖለቲካና ታሪክ እንደ አዲስ የሚበይን ፤ የሀገሪቱን ሕልውና በጽኑ መሠረት ላይ የሚያኖር እና መጻዒ ዕድሏን ወገግ የሚያደርገው ነው። በሰላሙ ግንባር ለተመዘገበው ድል የእሳቸው፣ የደጀኑ ሕዝብና በየደረጃው ያለው ወታደራዊና ሲቪል አመራር የተንሰላሰለና የተቀናጀ ብልህ አመራር በመስጠቱ መሬት ላይ በተቀዳጀነው ወታደራዊ ድል የተገኘ መሆኑን ከፍ ብሎ ለመግለጽ ተሞክሯል።

በአጠቃላይ ለቀጣይ ልማታችን ዋንኛ መሠረት የሆነውን ሰላማችንን በግርግር እንዲመጣ በየትኛውም መልኩ አስተዋፅዖ ያደረጉ አካላት ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል፤ በዚህም በተለመደ የማመስገን ባሕላችን ከልባችን እናመሰግናለን። ለሰላማችን ያበረከቱልን ጥልቅ አስተዋፅዖ በሰላም ግንባታ ታሪካችን ውስጥ ከፍ ያለ ስፍራ ይኖረዋል። መኃልየ-መኃልይ ዘ ሰላም ጀግና!።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የመተግበሪያዎች ልማት፣ተግዳሮቶችና መፍትሔዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ቴክኖሎጂ የሰው ልጅ ዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ አጋዥ በመሆን ጊዜን ፣ጉልበትንና ውጪን የሚጠይቁ ሂደቶችን ቀላል፣ፈጣንና ምቹ እያደረገ ይገኛል። ቴክኖሎጂ እያንዳንዱ የዓለም እንቅስቃሴ እየተቆጣጠረ ባለበት በዚህ ዘመን ከቴክኖሎጂ ውጭ መሆንም አይታሰብም።

በተለይ አሁን እየበለጸጉ የሚገኙት መተግበሪያዎች የቴክኖሎጂውን እድገት እያፋጠኑት እንደሆነ ይነገራል። በሀገራችንም በርካታ መተግበሪያዎች እየበለጸጉ አገልግሎት ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። በዛሬው ሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችንም "የእነዚህ መተግበሪያዎች መበራከት ፋይዳው ምንድነው?" ስንል የዘርፉን ባለሙያዎች አነጋግረን ያዘጋጀነውን ዳሰሳ ይዘንላችሁ ቀርበናል።

አቶ መርዕድ በቀለ የአይ ኢ ኔትወርክ ሶሉሽን መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የሞባይል መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽኖች) ሥራዎችን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒዩኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) በሲስተም እንዲመሩ የሚያስችሉ አማራጮች የያዙ መሆናቸውን ያብራራሉ። "የሞባይል መተግበሪያዎች የሚበለፅጉበት ዓላማ ውስን አገልግሎትን ለመስጠት ነው" በማለትም፤ ለምሳሌ ያህል የትራንስፖርት መተግበሪያ ከሆነ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማግኘት የምንጠቀምበት፤ የግብርና መተግበሪያ ከሆነ ደግሞ ግብርናን የተመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት፤ የሕክምናም መተግበሪያ ከሆነ ከሕክምና ጋር የተያያዙ ነገሮች ለማግኘት የሚውሉ እንደሆኑ ያብራራሉ።

መተግበሪያዎቹ እንደየዘርፉ አይነትና ባሕሪ የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የሚጠቅሱት ሥራ አስፈፃሚው፤ ለእያንዳንዱ ዘርፍ የሚበልጸጉት መተግበሪያዎችን ሞባይል ስልክ ላይ ስለሚጫኑ ሰዎች ለሚፈልጉት አገልግሎት የሚጠቀሙበትን መተግበሪያ ብቻ በመጫን መጠቀም እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

"ለእያንዳንዱ አገልግሎት የሚያስፈልገው የራሱ የሆነ መተግበሪያ አለ" የሚሉት አቶ መርዕድ፤ ለአብነት የቴሌ ብር መተግበሪያ ከክፍያ ጋር በተያያዘ አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ የቴሌ ብር ደንበኞች የሚጠቀሙበት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። ሁሉም ነገር ከወረቀት ሥራ እየወጣ በቴክኖሎጂ እየተደገፈ በመጣ ቁጥር አገልግሎቱን ሁሉም ሰው እንዲያገኝ ለማድረግ ሞባይል መተግበሪያዎች እየተፈጠሩ መምጣታቸውን ይጠቁማሉ።

አቶ መርዕድ እንደሚሉት ፤አሁን ላይ የመንግሥት አገልግሎቶችም ወደዚያ ሲስተም እየገቡ የሚሄዱባቸው ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው። ሌላው ዓለም ላይ እንደሚታየው የመብራት፣ የስልክ፣ የውሃ እና የመሳሰሉት አገልግሎቶች ክፍያዎች በሞባይል መተግበሪያው አማካይነት ይከፈላሉ። የሞባይል መተግበሪያው የወር ሂሳብ ያሳውቃል፤ ከዚያ ሂሳቡን ባለበት ሆኖ የሚከፍልበት ሲስተም ተዘርግቶለታል። የኢሚግሬሽን ፓስፖርት የሚፈልግ ሰውም እንዲሁ በፓስፖርት መተግበሪያ ላይ በማመልከት አገልግሎቱ ሲጠናቀቅ በአድራሻው ይላክለታል።

‹‹የመተግበሪያዎች ዋንኛ ግብ ሥራን ማቀላጠፍና ጊዜን መቆጠብ ነው›› ያሉት አቶ መርዕድ ፤ረጅም ጊዜ የሚወስድባቸውን ቢሮክራሲ የሚበዛባቸውን ነገሮች በሙሉ ወደ ቴክኖሎጂ በማምጣት ሰዎች በቀላሉ ቤታቸው ቁጭ ብለው ብዙ አገልግሎቶች በፍጥነት፣በቅልጥፍና በጥራት እንዲያገኙ የሚያደርጉ አማራጮች እንደሆኑ ይናገራሉ ።

ይህንን አገልግሎት በሞባይል ለመጠቀም ዋንኛ አስፈላጊ የሆነው ነገር ኢንተርኔት እንደሆነ የሚገልጹት አቶ መርዕድ፤ ‹‹እኛ ሀገር ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ገና በመሆኑ ሰዎች ዳታ ሲጠቀሙ ይቆጥርብኛል ብለው ስለሚፈሩ እያበሩና እያጠፉ የሚጠቀሙት ሁኔታ አለ። መጀመሪያ ሰዎች ከዚህ መውጣት አለባቸው›› ይላሉ። ቀጥሎ ሁሉም የሞባይል ዳታዎች 4ጂና 5ጂ የሚባሉት ሁሉም ቦታ ተደራሽ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያመለክታሉ። በሌላው ዓለም ላይ ኢንተርኔት ተደራሽ ከመሆኑም ባሻገር የዳታ ዋጋም የሰዎችን አቅም ያገናዘበና ሁልጊዜም ክፍት ስለሚሆኑ ሰዎች የሚፈልጉትን መተግበሪያ በሞባይላቸው እንዲጭኑ ይረዳቸዋል፤ይሄም አገልግሎቶችን ሳይቆራረጡ እንዲያገኙ እንደሚያግዛቸው ያመለክታሉ።



ወጣት ሳምራዊት ታረቀኝ



አቶ መርዕድ በቀለ

አቶ መርዕድ እንደሚሉት፤ መተግበሪያዎች በስፋት በኢትዮጵያ አገልግሎት መስጫ አማራጭ ሆነው ከመስፋፋታቸው አስቀድሞ መጀመሪያ የቴሌኮም አገልግሎት አሰጣጥ በደንብ መስፋፋትና የኢንተርኔት ዋጋ ርካሽ ሆኖ ሰዎች በሚችሉት አቅም መጠን የሚያገኙት መሆን እንዳለበት ያነሳሉ። ይህ ሲሆን የሶፍትዌር ካምፓኒዎችና መተግበሪያዎችን በማበልፀግ የሚያስተዋውቁ አካላት እንደሚያበረታቱ ይጠቁማሉ።

የኢንተርኔት ዋጋ ውድ በመሆኑ መተግበሪያዎችም ቢበልጽጉ የሚጠቀምባቸው ሰው ከሌለ ያበለጸጉት ሰዎች ክፍያ አያገኙም በማለትም መተግበሪያ ማልማቱ ቀጣይነት እንዳይኖረው እክል እንደሚፈጥር አቶ መርዕድ ያስረዳሉ። ያበለጸጉት ሰዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ደግሞ ተጠቃሚው ብዙ መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ። ስለዚህ የኢንተርኔት ዋጋ መቀነስና ተደራሽነቱም መጨመር አለበት በማለት ምክረ ሃሳባቸውም ይሰጣሉ። ለዚህ ደግሞ ኢትዮ ቴሌኮም ሆነ ሳፋሪኮም ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል የሚል መልእክት ያስተላልፋሉ።

ቴክኖሎጂ ዓለም አቀፋዊ በመሆኑ ማንም ሰው ኢንተርኔት ላይ የሚያገኛቸውን ነገሮች መነሻ በማድረግ የተለየ ፈጠራ ሳያስፈልገው የሚሠራበት ሁኔታ መኖሩን የሚናገሩት አቶ መርዕድ፤ ሌላው ዓለም ላይ መነሻ የሆኑ ፕላትፎርሞች ስላሉ ችሎታ ያለው የሰው ኃይልና ሰፊ የገበያ ተደራሽነት ካለ ብዙ ችግሮች በቀላሉ መቅረፍ እንደሚችል ይገልፃሉ።

የተማረ ኃይል በበቂ ሁኔታ ገበያው ላይ እየቀረበ አለመሆኑን የሚገልፁት ዋና ሥራ አስፈፃሚው ‹‹እንደ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያ የምናበለፅጋቸው ሶፍት ዌሮች ለቢዝነሶች የሚሆኑና ሥራ ሊያቀላጥፉ የሚያስችሉ ናቸው። ከኛ ልምድ ስንነሳ ትልቁ ችግር ችሎታ ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ብዙ የለም›› በማለት በሰው ኃይል በኩል ያለውን ችግር ይጠቁማሉ። ከዩኒቨርሲቲዎች በኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ(Ict)፣ ከኤሌክትሪካልና ኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ያላቸው መነሻ ነገር መሆኑን ጠቅሰው፤ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎችን እንደኛ ያሉ የግል ካምፓኒዎች እውቀታቸው የበለጠ እንዲያድግ መልሰው ማሰልጠን ይጠበቅባቸዋል። ከዩኒቨርሲቲ ብቻ የሚያገኙት እውቀት በፍጥነት ውጤት እንዲያመጡ አያደርጋቸውም ይላሉ።

እነዚህ መተግበሪያዎች እንዲስፋፉ መንግሥት በፖሊሲ ደረጃ ቁርጥ ያለ አቋም በመያዝ የመንግሥት አገልግሎቶችን በሙሉ በቴክኖሎጂ ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባውም ነው የሚጠቁሙት። ለአብነት የሌላውን ዓለም ተሞክሮ ብንመለከት ቤት መግዛት፣ መሸጥና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን መንግሥት ቢሮ መሄድ ሳያስፈልግ እያንዳንዱ ነገር በመተግበሪያ የሚያልቅበት አሠራር ተዘርግቶ ፤ለመፈራረም እንኳን ውልና ማስረጃ መሄድ ሳያስፈልግ ሲስተም ላይ ኦንላይን መፈረም የሚችልበት አሠራር ተቀምጧል። በኛ ሀገር ብዙ ሰው እሮሮ ያለበት ፤ እንግልት የበዛበት አሠራር በቴክኖሎጂ በመተካት ብዙ የመንግሥት አገልግሎቶች መቀላጠፍ እንደሚችሉ አስታውቀዋል።

‹‹የግል ሴክተሩ አልታገዘም እንጂ አሁንም ጥረት እያደረገ ነው›› የሚሉት አቶ መርዕድ፤ የግሉ ሴክተር አጋጣሚውን በመጠቀም ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ሥራዎችን ለማቀላጠፍ ሰፊ ርብርብ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አንስተዋል። የፋይናንስ ዘርፉም ስታርትአፖችን፣ አነስተኛና መካከለኛ የሆኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ካምፓኒዎችን የማገዝ ባሕሉ መዳበር እንዳለበት ይጠቁማሉ።

‹‹የሞግዚት ዶት ኮም›› መተግበሪያ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወጣት ሳምራዊት ታረቀኝ በበኩሏ የአቶ መርዕድን ሀሳብ በመጋራት ዝቅተኛ የኢንተርኔት ተደራሽነት፣ የኢንተርኔት ዳታ ውድነት፣ መተግበሪያዎች እንዳይስፋፉ የሚያደርጉ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ታነሳለች።

ቴክኖሎጂን መጠቀም ቅንጦት አይደለም በማለትም፤ ቴክኖሎጂ በሁሉም የሀገሪቷ አካባቢዎች ተደራሽ መሆንን ይዞ የመጣ መልካም እድል መሆኑን ጠቅሳ፣ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ትላለች። በተለይ በዚህ ዘርፍ በየዓመቱ ለሚመረቁ በርካታ ተማሪዎች የዲጂታል ዘርፍ ትልቅ ተስፋ መሆኑንም ትገልጻለች። ተመራቂዎች ቁጭ ብለው ሥራ ከመጠበቅ የራሳቸውን ቢዝነስ ፈጥረው መንቀሳቀስ እንደሚያስችላቸው ጠቅሳ፣ ለብዙዎች የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል እንደሆነ ትናገራለች።

ወጣት ሳምራዊት ታረቀኝ እንደምትለው፤ ዲጅታል ኢኮኖሚ ብዙ ዘርፎች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ኢኮሜርስ ሲሆን፣ ይህም በበይነመረብ የሚፈልግን አንድ አገልግሎት ወይም ምርት ለማግኘት የሚጠቅም የመገበያያ መንገድ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በአጭር ጊዜ ተቀባይነት ያገኘና እያደገ ያለ አንድ የመገበያያ ዘርፍ ነው። ብዙ ተግዳሮቶች ያለበት ይህ ዲጂታል ኢኮኖሚ፣ በኢትዮጵያ በየዓመቱ 18 በመቶ ያህል እድገት አሳይቷል ትላለች። ይህ ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ በዲጂታል ኢኮኖሚው ስለመሥራት እንድናስብ እንደሚያደርግ ትገልጻለች።

ከተግዳሮቶቹ በላይ ያሉ እድሎች አብረውት እየመጡ ነው የምትለው ሳምራዊት፤ እንደሳፋሪኮም ያሉ የቴሌኮም ካምፓኒዎች መግባታቸው ተፎካካሪነትን በመፍጠር የኢንተርኔት ተደራሽነትን እንዲሰፋ ያደርጋሉ ትላለች። አሁን ዲጂታል የክፍያ ሥርዓቶች ተፈጥረዋል፤ በኦንላይን /በቀጥታ/ መክፈል የሚቻልባቸው መንገዶች እየበዙ እና እየተለመዱ ነው ስትል ገልጻ፣ እንደ ቴሌብር አይነቶቹ የተለያዩ የመክፈያ ሥርዓቶች መፈጠራቸው ግብይቱን ቀልጣፋ እንደሚያደርጉ ትጠቅሳለች። ቀደም ሲል ቴክኖሎጂው ተደራሽ ቢደረግም የክፍያ ሥርዓቱ ግን እጅ በእጅ ይደረግ እንደነበር አስታውሳ፤ አሁን ግን የክፍያ ሥርዓቶች በዲጅታል መልኩ መፈጸማቸው የዘርፉን እድገት ያሳያል ትላለች።

አዲስ አበባ ውስጥ አገልግሎቶችን በኦንላይን ማዘዝና መቀበል እየተለመደና አንድ የሕይወታችን አካል እስከመሆን ደረጃ ደርሷል የምትለው ሳምራዊት፤ ኅብረተሰቡ ካለው የተጣበበ ጊዜ አንጻር ወደዚህ ሥርዓት በመግባት ተጠቃሚ እየሆነ ይገኛል ትላለች። ከአራት ዓመት በፊት የነበረው የአኗኗር ባሕል እየተቀየረ መምጣቱን ጠቁማ፣ ዲጂታል አገልግሎት ተጠቅሞ መገበያየት እየተለመደና ተመራጭ እየሆነ እንደሚገኝ አስታውቃለች። ሁኔታው ከዚህ በኋላ ለሚመጡም ሆነ እያደጉ ላሉ ኮምፓኒዎች ትልቅ የሆነ መነቃቃትን የሚፈጥር እንደሆነ ትገልጻለች።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ የሥራ እድል ለመፍጠር እንደ አንድ እድል የሚቆጠር ነው የምትለው ሳምራዊት፤ ጎረቤት ሀገር ኬንያ ጋር በዚህ በኩል የማንወዳደርበት ደረጃ ላይ ነን ትላለች። እሷ እንደምትለው፤ ኬንያውያን በዘርፉ ዓመታዊ ገቢያቸው ከፍተኛ ነው። የሕዝቡ ዲጂታል ቴክኖሎጂ የመጠቀም ባሕል ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኬንያ ይሄዳሉ። ይህ ደግሞ የውጭ ምንዛሪያቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል። በግብርና፣ በጤና፣ በቱሪዝም ሴክተሮችና በመሳሳሉት መድረስ የማንችልባቸው ቦታዎች ሁሉ ተደራሽ እንድንሆን ለማድረግ መሥራት ያስፈልጋል ስትል ታስገነዝባለች። የመንግሥት አገልግሎቶች በኦንላይን እየሆኑ፣ አገልግሎቶች እየተቀላጠፉ በቀላሉ ተደራሽ የሚደረጉበት ሁኔታ በደንብ ተጠናክሮ ሊሠራበት እንደሚገባም ትጠቁማለች።

እንደ ወጣት ሳምራዊት ገለጻ፤ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ማኅበረሰቡ ያለው ችሎታ ገና የሚባል ነው፤ ይህን ችሎታ ለማሳደግ ግንዛቤ ማስጨበጫዎችንና ሥልጠናዎችን መስጠት ያስፈልጋል። የኢንተርኔት ተደራሽነት በሌለባቸው ቦታዎች ማኅበረሰቡ ኢንተርኔት መጠቀም የማይችል ከሆነ ጎን ለጎን የሚሄድ ሲስተም መፍጠር ይገባል።

መተግበሪያዎች በመጠቀም የዲጂታል አገልግሎት ማግኘት በእጅጉ እረፍት ይሰጣል የምትለው ሳምራዊት፣ ‹‹እኔ ቴክኖሎጂ መጠቀም መጀመሬ ሥራዬን በጣም አቅልሎልኛል ትላለች። በየወሩ የሚጠበቅብኝን ክፍያ በኦንላይን አሳውቃለሁ፤ የምከፍለውም በኦንላይን ሲሆን፣ ደረሰኙም በኦንላይን ይመጣልኛል›› ትላለች።

ሥራ እያቋረጡ ሄዶ ወረፋ ጠብቆ መክፈል የሚለው ነገር መቅረቱን ጠቅሳ፤ ቴክኖሎጂ በጣም በቀላሉ ሥራዎችን ማቀላጠፍ እንደሚያስችል ትናገራለች። በቴክኖሎጂ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ለመጠቀም ቴክኖሎጂውን አዳብሮ ሰዎች በቀላሉ ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ለማድረግ ማስፋፋት ላይ መሥራት እንደሚገባም ጠቁማለች። መተግበሪዎች ሲሠሩ በቅድሚያ ተገልጋዩ መታወቅ አለበት ትላለች። ኅብረተሰቡ በቀላሉ ሊገለገልባቸው የሚችሉ፣ በዝቅተኛ የኢንተርኔት ዋጋ የሚሠሩ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር እንደሚገባ አስገንዝባለች።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የፕሮጀክቶች መዘግየት ምጣኔ ሃብታዊ እና ፖለቲካዊ አንድምታ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በሰጡት ማብራሪያ፤ በአገሪቱ በተለያዩ ወቅቶች የተጀመሩና በአሁኑ ወቅትም በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አገሪቱን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጓት መሆኑን አብራርተዋል።ለአብነትም በጅምር ያሉትን 320 የመንገድ ፕሮጀክቶችን ብቻ ለማጠናቀቅ ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ እንደሚያስፈልጋት አስገንዝበዋል።ከዚህም በተጨማሪ ሀገሪቱ ከፍተኛ ዕዳ ያለባት በመሆኑ በልማት ላይ ጫና እየፈጠረ መሆኑንና መንግሥትም ዶላር ማመንጨት ላይ እየተፈተነ ስለመሆኑ አስረድተዋል።ለመሆኑ ፕሮጀክቶች ለምን ይዘገያሉ? ሲዘገዩስ በአንድ አገር አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ሊፈጥሩ የሚችሉት ጉዳት ምን ያህል ነው? በሚለው ላይ ምሑራን ምልከታቸውን ያጋራሉ።

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር አረጋ ሹመቴ፣ በሀገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ማጠናቀቅ ማለት በአገሪቱም ላይ ያንዣበቡ ምጣኔ ሃብታዊ ችግሮች ፈጣን እልባት እንደመስጠት ይቆጠራል ይላሉ።ፕሮጀክቶች በፍጥነት እየተጠናቀቁ ነው ማለት የአንድ ሀገር የኢንቨስትመንትና የማድረግ ብቃት የሚለካበት መስፈርት መሆኑንን ይናገራሉ።ይሁንና በኢትዮጵያ እየሆነ ያለው ከዚሁ ተቃራኒ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።ፕሮጀክቶች ሲዘገዩ በራሱ የአንድን ፕሮጀክት እይታ ብቻ ሳይሆን ሌላውን የሚነካ ይሆናል።ሜጋ ፕሮጀክቶች በዘገዩ ቁጥር የሚፈጥሩት ጫና ዘርፈ ብዙ መሆኑን ያብራራሉ።

የፕሮጀክቶች መዘግየት የዋጋ ግሽበትን በማባባስ ረገድ ሚናቸው የጎላ ነው የሚሉት ዶክተር አረጋ፣ መሰል ፕሮጀክቶች በፍጥነት የማይጠናቀቁ ከሆነ ከፍተኛ ገንዘብ የሚወስዱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በየጊዜው አዳዲስ በጀት የሚያዝላቸው በመሆኑ ለሌላ ፕሮጀክት መዋል የነበረበት ገንዘብ ለአንድ ፕሮጀክት ይውላል፤ ይህ ደግሞ የዋጋ ግሽበትን በማስከተል የራሱን ሚና ይጫወታል ይላሉ።የመንግሥትን የበጀት ጉድለት ከማባባስ አኳያም ድርሻ እንዳለው የሚናገሩት ዶክተር አረጋ፣ ለሚዘገዩ ፕሮጀክቶች ተብሎ በጀት ሲበጀት መንግሥትን ላልተፈለገ ወጪ እንደሚዳርግና ይህ ደግሞ የበጀት ጉድለት ከሚያስከትሉ አንኳር ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀስ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

ሜጋ ፕሮጀክቶች በዘገዩ ቁጥር ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን በመፍጠር የምጣኔ ሀብትን ከሚያመሳቅሉት ምክንያቶች መካከል በቀዳሚነት እንደሚጠቀስ የሚናገሩት ዶክተሩ፣ በኢትዮጵያ በየጊዜው አዳዲስ ፕሮጀክቶች እየተጀመሩ መሆናቸውን እንጂ በፍጥነት ስለመጠናቀቃቸው ጥርጣሬ እንዳላቸው ያመለክታሉ።እነዚህ ፕሮጀክቶች ደግሞ በአብዛኛው የሚጠቀሙት ግብዓት የሚመጣው ከሀገር ውጭ ሲሆን፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንደሚፈልጉ ያብራራሉ።

በዓለም ላይ በፍጥነት ሁኔታዎች ተለዋዋጭ በሆኑበት አጋጣሚ ሁሉ የዶላር ምንዛሪም በተመሳሳይ ሁኔታ እየተቀያየረ የዓለም ምጣኔ ሃብትም በዚያው ልክ እየተለዋወጠ ነው።ታዲያ ኢትዮጵያን የመሰሉ ወደብ አልባ ሀገራት ደግሞ በመሰል ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቀዳሚዎቹ ተጠቂ ናቸው ይላሉ።ይህም ብቻ ሳይሆን ግብዓቶቹም ተጓጉዘው በፕሮጀክቶቹ ቦታ እስከሚደርሱ ድረስ ያለው አገራዊ የሰላምና መረጋጋት ሁኔታም አስተማማኝ ባለመሆኑ ነገሮች የበለጠ የተወሳሰቡ ያደርጋቸዋል፤ በዚህ ደግሞ አገር ዋጋ እየከፈለች ነው ሲሉም ያስረዳሉ፡፡

> ፕሮጀክቶችንም መጀመር ብቻ ሳይሆን የረጅም እና የአጭር ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ምንድን ነው የሚለው በሚገባ ማጤንና የጥናት ውጤቶችን በጥልቀት መመልከት ተገቢ ነው

ለአብነትም ለስኳር ፕሮጀክቶች ተብሎ 72 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጎ በታሰበው ልክ ውጤታማ ባለመሆናቸው ሀገሪቱን ለከፍተኛ እዳ ዳርጓታል።የባቡር ፕሮጀክቶችም ከአዋጭነታቸው ይልቅ አከሳሪነታቸው በጣም የጎላ ስለመሆኑ መንግሥት በራሱ ያመነው ጉዳይ ነው።በርካታ ቢሊዮን ብር ፈሰስ የተደረገባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶችም በታሰበው ልክ አገልግሎት ለመስጠት አልታደሉም፤ ለዚህም በአዲስ አበባ በአጭር ጊዜ ይጠናቀቃሉ ተብለው የተወጠኑ የመንገድ ፕሮጀክቶች ዓመታትን የዘለቀ ወቀሳ ማስከተላቸውን በዋቢነት ይጠቅሳሉ።እነዚህ ፕሮጀክቶች በአጭር እና በረጅም ጊዜ አገሪቱ ወደማትወጣው ምስቅልቅል ውስጥ ከሚያስገቡ የፕሮጀክት አመራርና አሠራር አንዱ መሆኑን ይጠቁማሉ።

እንደ ምሑሩ ገለፃ፤ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በስተቀር የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችም በትክክል ያሉበትን ደረጃ የሚገልፅ ሪፖርት አይሰማም፤ ጠያቂም የለም።በእነዚህ ላይም በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ ተደርጓል።መንግሥት ከእነዚህ ፈተናዎች ለመውጣት አማራጮች ላይ ማማተር አለበት።በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የግሉ ዘርፍ በብዛት እንዲገባበትና የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ብሎም የአገሪቱን የምጣኔ ሃብት እንዲያድግ መሥራት ያስፈልጋል።የዘገዩ ፕሮጀክቶችን በፍጥነት ለማጠናቀቅ ይረዳ ዘንድም ቁርጥ ያለ ፖለቲካዊ አመራር እና ውሳኔ ሰጪነት የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡

በሌላ ጎኑ ደግሞ በርካታ ፕሮጀክቶችን በአንድ ጊዜ ከመጀመር ይልቅ ስልታዊና አዋጭ ተብለው የተለዩ አካሄዶችን መከተል እንደሚገባ ይጠቁማሉ።ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች በመለየትና የአሠራር ሥርዓታቸውንም ሳይንሳዊ ብሎም ከፖለቲካ ጫና የፀዳ በማድረግ፤ ጠንካራ አመራር በመስጠት ችግሮችን ማቃለል ይቻላል፡፡

በሌላ ጎኑ ደግሞ በብዛት እየዘገዩ የሚገኙት ፕሮጀክቶች በመንግሥት የልማት ድርጅት ስር የሚከወኑ ወይንም የሚተዳደሩ አሊያም ደግሞ በመንግሥታዊ ተቋማት የሚመሩ ናቸው።በመሆኑም እነዚህን ፕሮጀክቶች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ አንዱ ሌላውን መደገፍ አለበት ይላሉ።ለአብነትም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሌሎች የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በመደገፍ ብቁና ተወዳዳሪ ማድረግ የሚቻልበትን መላ መምታትም ሌላኛው መንገድ ስለመሆኑን ያብራራሉ።

ቀደም ሲል በባንክ ዘርፍ ውስጥ ያሳለፉትና በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክት በመምራት ላይ ያሉት አቶ ታምራት ዓለሙ በበኩላቸው፤ የፕሮጀክቶች መዘግየት በሀገሪቱ ላይ ዘርፈ ብዙ ጉዳት ያደርስባታል የሚለውን የዶክተር አረጋን ሐሳብ ይጋራሉ። ፕሮጀክቶች ሲዘገዩ ምጣኔ ሃብታዊ አንድምታው ጎልቶ ይውጣ እንጂ ጉዳቱ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስን ጭምር የሚያስከትል መሆኑንም ያብራራሉ።

ፕሮጀክቶች በዘገዩ ቁጥር ሥራ ዕድል ፈጠራ በማዘግየትና በርካታ ሥራ አጦችን እንዲፈጠሩ በማድረግ የበኩሉን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።ይህ ደግሞ ሥራ አጦች በበዙ ቁጥር ሀገሪቷን ወደአልተፈለገ አቅጣጫ የመውሰድ ዕድል እንዲኖረው ያደርጋል።ራስን በመቻል እና በዓለም የዕድገት የደረጃ ሰንጠረዥ ውስጥ የሀገራትን ደረጃ ዝቅ የሚያደርግ በመሆኑም እንደ ሀገር የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።ሀገራት በብዛት የዲፕሎማሲ አቅማቸውን ለማሳየት ከሚጠቀሙት ዋንኛው ምጣኔ ሀብት በመሆኑ ሜጋ ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በማጠናቀቅ ወደ ሥራ ማስገባት ማለት ምንም እንኳን ሌሎች የዲፕሎማሲ ተጽዕኖ መፍጠሪያ አማራጮች ቢኖሩም፤ ዲፕሎማሲን በፈለጉት መንገድ ለማሳለጥ ሰፊ እድል ይሰጣል፡፡

ይሁንና አቶ ታምራት፣ በአንዳንድ መልኩ የዶክተር አረጋን ሃሳብ ይቃወሙታል።ምንም እንኳ እነዚህ ፕሮጀክቶች የሀገር ምጣኔ ሃብት ላይ የሚኖራቸው ሚና በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም፤ አንዱ እስኪጠናቀቅ ሌላውን ማዘግየት ወይንም ደግሞ አለመጀመር በራሱ ጉዳት አለው ይላሉ።ፕሮጀክቶች ሁሉ በአንድ ላይ እንደማይጀመሩ ሁሉ በአንድ ጊዜም ማጠናቀቅ አይቻልም።ከዚህ በተጨማሪም የአንድ ፕሮጀክት የገንዘብ ምንጭ በአገሪቱ አቅም ወይንም ከመንግሥት ካዝና የሚመጣ ሊሆን ይችላል፤ ሌላው ደግሞ የገንዘብ ምንጬ ብድር ወይንም በእርዳታ የሚገኝ ስለሚሆን አዳዲስ ፕሮጀክት ለመጀመር ወይንም ለመጨረስ እንደቅድመ ሁኔታ መቀመጥ ያለበት ፕሮጀክት መብዛት መሆን የለበትም ባይ ናቸው።ይልቁንም ፕሮጀክቶቹን ለማጠናቀቅ ምን ዓይነት መንገዶችን መከተል ይገባል? የገንዘቡ ምንጭስ ምንድን ነው? የሚለው ላይ በደንብ ማውጠንጠን ይገባል ይላሉ።

ሌላው አንደኛው የመንግሥት የልማት ድርጅት ሌላኛውን መደገፍ አለበት የሚለው ምክረ ሃሳብም ብዙም አያስኬድም ባይ ናቸው።ምክንያት ደግሞ አንዱ ሌላኛውን ሲደጉም ምናልባትም ካለበት ሊንሸራተት እና አፈፃፀሙንም ቀርፋፋ ሊያደርገው ይችላል።ለአብነትም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሥመ ገናና እና ተወዳዳሪ ተቋም ነው።ይሁንና ይህ ተቋም ሌሎች የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን መደጎም ወይንም ማገዝ ቢጀምር ትኩረቱ ሊበታተን ይችላል የሚል ስጋት አላቸው።ይልቁንም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቀደም ሲል ይተዳደሩበት ከነበረው ዕይታ ወጣ በማለት በሌላ መንገድ ማስተዳደር እና ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ ማመንጨት የሚችሉበትን ስልት መንደፍ ተገቢ ይሆናል።ለእዚህም ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መቅሰም እና ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማስተሳሰር እንደሚገባም ይመክራሉ፡፡

ምሑራኑ፣ የፕሮጀክቶች መዘግየት የአንድን አገር የመፈጸም አቅምን በሚገባ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይና የተወዳዳሪነት አቅም የሚለካበት ስለመሆኑ ይስማማሉ።በተለይም ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ በምጣኔ ሃብት ተወዳዳሪ የመሆን አንዱ መለኪያ ሜጋ ፕሮጀክቶች በፍጥነትና በጥራት በማጠናቀቅ ወደሚፈለገው ምርታማ ሂደት መቀየር ነው።ይህን ያሳኩ ሀገራት በዓለም ላይ ጫና እየፈጠሩ ነው።ከዚህ በዘለለ ፕሮጀክቶችን የማስተዳደር ስልት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚስተዋለው የሜጋ ፕሮጀክቶች አጀማመር፣ የግንባታ አካሄድና ውጤታማ የማድረግ ሂደት በብዙ መንገድ ወደኋላ የቀረ በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚያሻው ነው።

መንግሥት መሰል ፕሮጀክቶችን ከመጀመሩ በፊት ደጋግሞ ማሰብ እንደሚጠበቅበት የሚናገሩት ምሑራኑ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ ሀገር አዲስ ፕሮጀክቶችን ማስተዳደር ባሕል ሊዳብርና ከውጪው ዓለም በቂ የሚባል ልምድ መቅሰም እንደሚገባ ያሳስባሉ።ፕሮጀክቶችንም መጀመር ብቻ ሳይሆን የረጅም እና የአጭር ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ምንድን ነው የሚለው በሚገባ ማጤንና የጥናት ውጤቶችን በጥልቀት መመልከት ተገቢ ነው።የፕሮጀክቶች መዘግየት ዘርፈ ብዙ አንድምታዎች ያሉት በመሆኑም መንግሥት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባም ምሑራኑ አበክረው ያሳስባሉ።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 1 ሺ 647 ሴቶች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሰላማዊት ውቤ**

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደ አገር የሚጫወተውን ሚና ለማጉላት በአዲስ መልክ ከተዋቀረ ዘንድሮ ዓመት ከመንፈቅ ሆኖታል። አወቃቀሩ በአገር አቀፍ ደረጃ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ ፣ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀምና ሥራን ለማቀላጠፍ አግዞታል፤ ለሌሎች ባለድርሻ አካላትም ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

ከአዲሱ መዋቅር ወዲህ ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 1 ሺ 647 ሴቶች በቀጥታ የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል። 547 ሺ 927 ሴቶች ደግሞ በገቢ ማስገኛ የሥራ መስኮች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል። ከተሰጠው ሰፊ ኃላፊነት አንፃር በዓመት ከመንፈቁ ውስጥ ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ያከናወነው ስራ ‹‹አባይን በጭልፋ የመዝገን›› ያህል ቢሆንም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሰረት በ2014 ዓ.ም 38 ሚሊዮን 738 ሺ 181 የሚሆኑ ወጣቶችን በልዩ ልዩ የስራ መስኮች ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።

በተለይ 19 ሚሊዮን 206 ሺ 442 ለሚሆኑ ሴት ወጣቶች በችግር ምክንያት ከትምህርት ገበታ እንዳይስተጓጎሉ የትምህርት መርጃና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ከማቅረብ ጀምሮ በልዩ ሁኔታ እያበቃ መገኘቱ ትልቅ እምርታ ነው። ይህም ሴት አመራሮችን ማፍራትን ያካትታል።

ከዚህ ባሻገር ግን ሚኒስቴር መሥርያ ቤቱ በዚህ ጊዜ ውስጥ በተለይም በስድስት ወር አፈፃፀሙ ወቅት መዋቅራዊ አደረጃጀቱ እስከ ክልልና ከተማ አስተዳደር አለመውረድና በአዲስ አበባ ጎዳና የሚወጡ ዜጎች ቁጥር መበራከት ከገጠሙት ችግሮች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው። ለቀውስ የሚያጋልጡ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ታቅደው ስለማይመጡ በጀት መፈለጋቸውና ለበጀት ዓመቱ ደግሞ የተያዘው ዕቅድ በሰው ኃይል ስምሪት ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀርምና ይህንን በቀጣይ በሌላ ዕቅድ ለማካተት እየሰራ ይገኛል። በዚሁና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ የሚከተለውን ማብራሪያ ለአዲስ ዘመን ሰጥተዋል።

ኃላፊዋ እንደሚሉት፤ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መላው የሀገሪቱን ዜጎችን እያገለገለ ይገኛል። ሴቶችን፣ ህፃናትን፣ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ወጣቶችን እንደዚሁም ለተለያየ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መብት በማስከበር፤ ሁለንተናዊ ተሳታፊነታቸውን ያረጋግጣል። በኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ተጠቃሚ እንዲሆኑም ያደርጋል። ከችግሩ ስፋት አኳያም በየዓመቱ በተያዘው ዕቅድ መሰረት እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊና ተጠቃሚና ለማድረግ ብሎም ለመብታቸው ስራዎች እየተሰሩ ነው። አደረጃጀቱም ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ሚናውን ለመወጣት የሚያስችለው ነው።

ኃላፊዋ እንደሚናገሩት፣ አሁን ባለው አደረጃጀት የሴቶችም፣ የወጣቶችም፣ የአካል ጉዳተኞችም ማህበራዊ ጉዳይ ነው የሚባለው። በፊት በነበረው አደረጃጀት ግን የሴቶች፣ የወጣቶችና ህፃናት ዘርፎች ለየብቻቸው ሆነው ነበር ስራቸውን የሚያከናውኑት። ይህም ለአገልግሎት አሰጣጥ አስቸጋሪ ነበር። ሆኖም በአንድ መጠቃለሉ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ለመስራት አስችሏል። ለባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎም ምቹ መደላድልን ፈጥሮላቸዋል። ለሀብት አጠቃቀም ጥሩ ሁኔታ ፈጥሯል። ተጠቃሚውም ከአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲያገኝ አስችሎታል።

ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ አሁን ባለው መንገድ ተደራጅቶ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ አንድ ዓመት ተኩል ሆኖታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። አደረጃጀቱም ለሀብት አጠቃቀምና ሥራን ለማቀላጠፍ አግዞታል። በፌዴራል ደረጃ ማህበራዊ ጉዳይ ፣ ሴቶችና ህፃናትና ወጣቶች በተለያዩ ሚንስቴር ዲኤታዎች ይመራሉ። በዚሁ መሰረት ሴቶች በሴትነታቸውና በወጣትነታቸው ተሳታፊና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ይሰራል። የሴት ወጣቶችን ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንፃር በሴትነታቸውና በወጣትነታቸው በኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። ስራውም በዕቅድ ይከናወናል። ለአብነትም ሴቶች በወጣትነታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትምህርት ቤት ሲማሩ ለትምህርታቸው አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎች ይደረግላቸዋል። ድጋፉም የሚደረገው አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር ሲሆን በድርጅቶቹም ሴት ወጣቶቹ እንዳይቸገሩና በችግር ምክንያት ወደ ኋላ እንዳይቀሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ይቀርብላቸዋል።

በተጨማሪም ለሴቶች በተለየ መልኩ የሚያስፈልጉ እንደ የንፅህና መጠበቂያ አይነት ግብአቶች ይቀርቡላቸዋል። ክልሎችም ከሴቶች ጉዳይ ጋር በተያያዘ በዕውቀት እንዲጎለብቱ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ይሰጣቸዋል።

ለችግር ተጋላጭ የሆኑና በሴተኛ አዳሪነት የተሰማሩ ወጣት ሴቶችም አሉ። ምንም እንኳን ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ በእዚህ ጉዳይ ላይ ባይሰራም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችል የክህሎትና የተግባር ስልጠና ይሰጣል። ስልጠና ሰጥቶ በቀጥታ በሥራ ዕድል ፈጠራ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ያደረጋቸው ችግረኛ ሴቶችም አሉ። በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 1 ሺ 647 ሴቶች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በገቢ ማስገኛ ሥራ መስኮቸ ላይ እንዲሳተፉም ተደርጓል።

ለማሳያም 547 ሺ 927 ሴቶች በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ መሰማራት የሚያስችላቸው ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ ገብተዋል። ወደ ሥራ መግባት የሚያስችላቸው ብድርም እንዲመቻችላቸው ተደርጓል። እንዲሁም በየወረዳውና በየክልሉ፣ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ያሉ ሴቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ ተሰርቷል። ተተኪ አመራሮችን ማፍራት የሴቶች ተጠቃሚነት አንደኛው ስራ እንደመሆኑ ከኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ጋር በመቀናጀት 1 ሺ 552 ሴቶች በሱሉልታ ማሰልጠኛ የተተኪ አመራርነት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። ያለ ዕድሜ ጋብቻ እንዳይፈፀምና ጾታዊ ጥቃት እንዳይደርስ ለማድረግም በየክልሉ ከወንድም ከሴትም የተውጣጣ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሰራ ይገኛል።

እንደ ኃላፊዋ ገለፃ በ2014 ዓ.ም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጄንሲ መረጃ መሰረት አጠቃላይ የሀገሪቱ ወጣት ቁጥር 38 ሚሊዮን 738 ሺ 181 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 19 ሚሊዮን 206 ሺ 442 ያህሉ ወይም 50 ከመቶው ሴት ወጣቶች ናቸው። በፊት በነበረው የወጣቶች ፖሊሲ ወጣት የሚባለው የእድሜ እርከን ከ15 ዓመት እስከ 29 ዓመት ነበር። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአፍሪካ ወጣቶች ቻርተር ላይ የፈረመበት የወጣቶች የእድሜ ክልልም ይኸው ነው።

ኢትዮጵያ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የወጣቶች ፖሊሲን እያሻሻለች ሲሆን በዚሁ ማሻሻያ ወቅት የሚወሰደው የዕድሜ ክልል በአፍሪካ ቻርተር የተቀመጠው ከ15 እስከ 35 ያለው ሲሆን በየመስኩ ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚደረጉት ሴት ወጣቶችም ዕድሜ ክልል ይኸው ነው። በዓመት አንዴ የሚከበረው የዓለም ሴቶች ቀንም እነዚህን ወጣት ሴቶችን ጨምሮ አጠቃላይ የሴቶችን ተሳታፊነት፣ መብትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል።

ብዙዎች በዓሉ ዳቦና ኬክ ከመቁረስና ከፈንጠዝያ ያለፈ ፋይዳ የሌለው ይመስላቸዋል። አደባባይ ወጥቶ ማክበሩም አስፈላጊ አይደለም ብለው የሚያምኑ አሉ። ነገር ግን ሥራው ግንዛቤ የማስጨበጥ የንቅናቄ ስራ በመሆኑ ከቢሮ ወጥቶ መስራትን ይጠይቃል። ሁሉም አካላት መሳተፍ ይኖርባቸዋል። በንቅናቄ ደረጃ በመሰራቱ በዓሉ አሁን ላይ የሁሉም ሆኗል። መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ እንዲሁም ሌሎች አጋር አካላትም በዓሉን ያከብሩታል።

በዓሉ መከበሩና አደባባይ መውጣቱ በሴቶች ላይ የነበረውን የአትችልም አስተሳሰብ አስተካክሏል። ይህን አስተሳሰብ መቀየር በመቻሉም ሴቶች በተለየዩ የኃላፊነት ደረጃዎች እየታዩ መጥተዋል። ከሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ጀምሮ የማይደፈሩ የስልጣን እርከኖችም በሴቶች እየተያዙ ነው። አትችልም የሚለውን አስተሳሰብ በዓሉን ለማክበር በሚደረግ ውይይት፣ በተደረጉ የተለያዩ የተሞክሮ ልውውጦችና በተሰሩ የአደረጃጀት ለውጦች መስበር ተችሏል።

ሴቷ እቤቷ ብትቀመጥ በተደራጀ መልኩ አደባባይ በመውጣት መብቷን ማስከብር አትችልም። በመሆኑም በዓሉ ሴቶች በተደራጀ አግባብ አደባባይ በመውጣት መብታቸውን የማስከበር ትልቅ ግንዛቤ አግኝተውበታል። በመደራጀት መብትን ማስከበር አስፈላጊ እንደሆነም አውቀዋል።



ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ

**በአንድ እጅ ማጨብጨብ ስለማይቻል የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ወንዶችን በጉዳዩ ማሳተፍ ያስፈልጋል። ሴት ብቻዋን ተሰብስባ እኩል ነኝ፤ እኩልነቴን በራሴ አረጋግጣለሁ ብትል ከወንዶች ተሳትፎ ውጪ አይሆንም። የሴቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን ከማረጋገጥ አንፃር የወንድ አጋርነት የግድ ነው።ያለበለዚያ የሴቶች ተጠቃሚነት በቀላሉ ሊሳካ አይችልም**

‹‹ከወንዶች ጋር በነበረ አንድ ስብሰባ ያልተደራጀች ሴት መብቷ አይከበርም ወይ? የሚል ጥያቄ መነሳቱን የሚያስታውሱት ኃላፊዋ፤ ሚኒስቴር መሥርያ ቤቱ መብታቸውን ለማስከብር ሲደራጁ እንጂ ካልተደራጁ ተደራሽ ሊያደርጋቸው እንደማይችልም ያስረዳሉ። ከዚህ አንፃር በዓሉ ሲከበር መደራጀት ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ሴቶቹ መገንዘባቸውን ይጠቅሳሉ። በዚህም መንግስታዊ የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በየዓመቱ ለሴቶች የእውቅና መድረክ እያዘጋጁ መሆናቸውን ይጠቁማሉ። የሚሰሩና አርአያ የሚሆኑ ሴቶችም በዓለም የሴቶች ቀን ብቅ እያሉ መምጣታቸውን ይጠቅሳሉ። ይህም ሌሎችም ሴቶች እነርሱን እንዲከተሉ እየገፋፋ መሆኑንም ይናገራሉ።

በቅርቡ በዓሉ በተከበረበት ሰሞን የዓለም የሴቶች ቀንን አስመልክቶ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ የተሰጣትና ተሞክሮዋን ስታካፍል በመገናኛ ብዙሃን ያየናት ሴት ማሳያ ናትም ይላሉ ኃላፊዋ። ይሄ መድረክ ባይመቻች ኖሮ ይህች ሴት በየትኛው መድረክ ነበር ልትወጣ የምትችለው ሲሉም ይገልጻሉ። በተጨማሪም በዚሁ በዓል ታሪክ ሰርተው የነበሩ ሴቶች ተሳትፏቸው እንዲዘከር መደረጉንም ይጠቁማሉ።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ በአንድ እጅ ማጨብጨብ ስለማይቻል የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ወንዶችን በጉዳዩ ማሳተፍ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን የሴቶች በዓል ሴቶችን በተለየ ሁኔታ የሚያጎላ ቢሆንም ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን ከማረጋገጥ አንፃር የወንድ አጋርነት የግድ ነው። ያለበለዚያ የሴቶች ተጠቃሚነት በቀላሉ ሊሳካ አይችልም። ሴት ብቻዋን ተሰብስባ እኩል ነኝ፤ እኩልነቴን በራሴ አረጋግጣለሁ ብትል ከወንዶች ተሳትፎ ውጪ አይሆንም።

በማህበራዊውና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ብሎም በስልጠናም ሆነ በሥራ ቦታ ከወንዶች ጋር አብሮ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ካልተሰራና ወንዶችን የመፍትሄው አካል ማድረግ ካልተቻለ ውጤት ማምጣት አይቻልም። በመሆኑም ለብቻ ተነጥሎ የሚመጣ ለውጥ የለምና በሴቶችም በወንዶችም አስተሳሰብ ላይ እኩል ስራ መሥራት ይገባል።

ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ባለፉት ስድስት ወራት አፈፃፀሙ ከገጠመው ችግር ውስጥ አንዱ መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ታች እስከ ክልል፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደር አለመውረዱ ነው። በየክልሎች ሴቶችና ህፃናት ፤ወጣቶችና ስፖርት በተናጥል የመደራጀት ችግር ይታያል። በዚህ አሰራር አንድ ክልል ላይ ስብሰባ ለመጥራት አራት ቢሮ መጥራት የግድ ይሆናል። ሪፖርት ለመሰብሰብም ተመሳሳይ ሁኔታ ይጠይቃል። አወቃቀሩ አንድ ወጥ አለመሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። ትልቅ ችግርም ፈጥሯል። ይህን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ማስተካከያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል ሀሳብ ቀርቧል። በዚህም አወቃቀሩ ይስተካከላል፤ ችግሩንም ይፈታል ተብሎ ይታሰባል።

ሁለተኛው ችግር ደግሞ ከጎዳና የሚነሱ ዜጎች ጉዳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ሲሆን ከጎዳና አንስቶ ለማስቀመጥ የሚያስችል መጠለያና ማገገሚያ ማእከል አለመኖርም ችግሩን ድርብ አድርጎታል። የተወሰነ መጠለያ ቢኖርም በየጊዜው ጎዳና ከሚወጣው የሕብረተሰብ ክፍል አንጻር የሚመመጣጠን አለመሆኑም ራሱን የቻለ ችግር ሆኗል። ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ በአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ቢሮ አማካኝነት ያስጠናውንና በመዲናዋ አዲስ አበባ ከ50 ሺ በላይ ጎዳና የወጡ ዜጎች እንዳሉ የሚያመለክተውን ጥናት መሰረት በማድረግ የመወያያ ጽሑፍ ተዘጋጅቷል። ጽሑፉም ለሚመለከተው አካል ቀርቧል። ፅሁፉ የቀረበበት ዓላማ ዜጎች በየጊዜው ጎዳና የመውጣት ጉዳይ የአንድ መሥሪያ ቤት ወይም ከተማ አስተዳደር ስላልሆነ ሁሉም ኃላፊነት እንዲወስድበት ማድረግ ሲሆን የክልል ፕሬዚዳንቶች በሙሉ ባሉበት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት የመጨረሻ እልባት ይገኝበታል ተብሎ ታስቧል። ‹‹ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ለሃምሳ ሰው ጌጥ›› እንደሚባለው ሁሉም ሰው በጉዳዩ ላይ ከተረባረበበት ሊቀንስ ይችላል። ትልቁ ነገር ችግሩን ከምንጬ ማድረቅ ነው። ከምንጩ ለማድረቅ አንደኛው መፍትሄ ከተሞችን እኩል ማስፋትና ማበልፀግ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቤተሰብ ላይ መሥራት ነው። ዜጎች ወደ ጎዳና የሚወጡት በተለያየ መንገድ እንደመሆኑ ቤተሰብ ላይ መሥራት ያስፈልጋል።

ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ለፍልሰቱም፤ ለጎዳና ሕይወቱም ምክንያት ስለሆኑ እነሱንም ተረባርቦ መቀነስ መፍትሄ ይሆናል። ለማህበራዊ ቀውስ የሚያጋልጡ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ለመቅረፍ ታቅደው ስለማይመጡ በጀት ይፈልጋል። በበጀት ዓመቱ የተያዘው ዕቅድ ላይም ተፅዕኖ ይፈጥራል። በሰው ኃይል ስምሪት ላይም ችግሮች ስለሚስተዋሉ ችግሮቹን በቀጣይ እቅድ አካቶ መስራት ያስፈልጋል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**አዲስ ዘመን አዲስ ሆኖ ብቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በየእለቱ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ለአንባቢዎች በማድረስ ዘመናትን ተሻግሯል። ዛሬም ድረስ ያለድካም የኢትዮጵያን ታሪክ እየሰነደ ዘልቋል። በእያንዳንዱ እርምጃው ምን ምን ጉዳዮችን ይዞ ወደ አንባቢ ይቀርብ ነበር ብለን ወደኋላ መለስ ብለን በአዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን እንዳስሳለን። 1960ዎቹ እና 70ዎቹ በጋዜጣው ለንባብ በቅተው ከነበሩ ጉዳዮች መካከል በኢትዮጵያ ከሐዳር አካባቢ ስለተገኘው የሰው ልጅ የቅሪት አካል፣ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ስለወጣው ፖሊሲ፣ በዘመነ ደርግ የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖቶች ቅያሪን አስመልክቶ ስለወጡ ተከታታይ ዘገባዎችን ጨምሮ እንዲሁም ከሕዝብ ወደ መንግሥትና ከሕዝብ ወደ ሕዝብ የጥያቄና የትዝብት አጀንዳዎችን ይዞ ከሚዘዋወረው ደብዳቤዎች ከተሰኘው ገጽ ላይ ቆንጠር በማድረግ አቅርበናል።**

### ከሐዳር አካባቢ የተገኘው የሰው አፅም 3.5 ሚሊዮን ዓመት ዕድሜ አለው ተባለ

አዲስ አበባ (ኢ.ዜ.አ) በወሎ ክፍለ ሃገር በአውላ አውራጃ ሐዳር በሚባለው አካባቢ የተገኘው የሰው አፅም ቅሪት ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዓመት ዕድሜ እንዳለው ተረጋገጠ።

የአፅሙ ቅሪት ይህን ያህል ረጅም እድሜ እንዳለው የተረጋገጠው ለጥናታዊ ምርምር ወደ አሜሪካን ሃገር ተወስዶ በባለሙያዎች ጥናት ከተካሄደ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ትላንት ለብሔራዊ ሙዚየም በተሰጠበት ወቅት ነው።

**ማክሰኞ ጥር 20 ቀን 1967 ዓ/ም**

### የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ የመን ግንኙነት በደም የተገነባ መሆኑ ተገለጠ

አዲስ አበባ -(ኢ.ዜ.አ) የኢትዮጵያ አብዮትና አንድነት ከአደጋ ለማዳን ጭቆናንና ብዝበዛን በመቃወምና የእብሪት ወረራን በመከላከል ለሶሻሊዝምና ለጭቁን መደቦች አሸናፊነት እንደ ኢትዮጵያ ሐቀኛ ልጆች ሁሉ የየመን ሕዝባዊት ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ጀግኖችም ሕይወትን ያህል ከፍተኛ ዋጋ በመክፈላቸው የሁለቱ ወዳጅ አገሮች ግንኙነት በደም የተለሰነ መሆኑን ጓድ ብርጋዲየር ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቋሚ ኮሚቴ አባልና የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ገለጡ። (አዲስ ዘመን ማክሰኞ ጥር 20 ቀን 1967 ዓ/ም)

### ለኤርትራ ክፍለ ሀገር የወጣውን ፖሊሲ ውሳኔ የሚቀበሉት ታጋዮችና ጭቁኖች ናቸው

ወጣት ታጋይ ሣራ መኮንን ከአራት ዓመታት በላይ በኤርትራ በረሃ በትግል በነበረችበት ወቅት ስላስተዋለቻቸው ሁኔታዎች ሁለተኛው ክፍል ነው። ሣራ መኮንን በንግግሯ ውስጥ በአንክሮ ከገለጠቻቸው ነገሮች መካከል አንደኛው የኤርትራ ጭቁን ሕዝቦችና የተቀሩት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የተሳሰረ መሆኑን የሚያሳስብ ነው። ከዚህም ሌላ ሣራ መኮንን የኤርትራ ሐቀኛ ታጋዮች ከተቀሩት የኢትዮጵያ ታጋዮች ጋር ሆነው ለኤርትራ ክፍለ ሀገር በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የተረጋገጠ መፍትሔ ሊያስገኙ እንደሚችሉ ገልጣለች።

አልፈው የሰፊውን ጭቁን ሕዝቦች ችግር ለማስወገድ በረሃ ገብተው እንደነበር ካወሳች በኋላ፣ ከእንግዲህም ቢሆን ለጭቁን ኤርትራ ሕዝብ ሰላም የሚገኘው በአብዮታውያንና በጭቁን ሕዝቦች ጥረት እንጂ እንደ ኢ-ኤል-ኤፍና መሣዮቹ ባሉት የፔትሮ ዶላር ተገዢዎችና የለየላቸው አድኃሪያን እንደማይሆን ገልጣለች።

**(አዲስ ዘመን እሁድ መስከረም 4 ቀን 1969 ዓ/ም)**

### የኢትዮጵያ ብር ኖት በቅርቡ ይለወጣል

ይህ የፊውዳልና የከበርቴ ሥርዓት ምልክትና ውክል ሆኖ የቆየው በኢትዮጵያ ብሮች ላይ የነበረው ምስል፣በመካሄድ ላይ በሚገኘው አብዮት(ተሐድሶ እንዲያገኝ በማድረግ) አዲስ የኢትዮጵያ ገንዘብ/ ብር ከጥቅምት 4 /1969ዓ/ም ጀምሮ ለሕዝብ ይወጣል።

### ባንኮች ከጥቅምት 4-8 ኖቶችን ብቻ ይለውጣሉ

(ኢ.ዜ.አ)- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የአዲስ ባንክ ከነ ቅርንጫፎቻቸው ጭምር ከጥቅምት 4 ቀን እስከ 8 ቀን 1969ዓ/ም ድረስ ባሉት ቀናት ውስጥ የኖቶችን መለወጥ አገልግሎት ብቻ እንደሚያበረታቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ትናንት አስታወቀ።

ብሔራዊ ባንኩ በሰጠው ተጨማሪ ማብራሪያ፤ አብዛኛዎቹ ባንኮች ከጥቅምት 9 ቀን እስከ ጥቅምት 19 ቀን 1969 ዓ/ም ድረስ ከቀትር በፊት የኖቶች መለወጥ ተግባር ብቻ የሚያከናውኑ ሲሆን፤ ከቀትር በኋላ ደግሞ መደበኛውን የባንክ አገልግሎት ያበረክታሉ።

**(አዲስ ዘመን እሁድ መስከረም 14 ቀን 1969 ዓ/ም)**

### አዲሶቹ የገንዘብ ኖቶች ሥራ ላይ መዋል ጀመሩ ሕዝቡ ተደስቷል

ስለ ባንኮች አቋምና ስለ ገንዘብ ኖቶች መለወጥ በወጡት አዋጆችና ደንቦች መሠረት የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወትና ገናናነት የሚያንጸባርቁት አዲሶቹ የብር ኖቶች ከትላንት ጥቅምት 4 ቀን 1969 ዓ/ም ጀምረው በመላ ኢትዮጵያ በአገልግሎት ላይ ውለዋል።

.................

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በየክፍለ ሀገሩ ባሉት ቅርንጫፎች ገቢ ያደረገው ከሰሜናዊው ክፍል 15 ሚሊዮን፣ ከመካከለኛው 18.8፣ ከደቡባዊው ክፍል 7.5 ሚሊዮን፣ ከምዕራባዊው ክፍል 7.1 ሚሊዮን፣ ከምሥራቃዊው ክፍል 13.5 ብር እንደሆነም አቶ ለገሰ ጥቃሄር አስታውቀዋል።

በሕዝቡ እጅ፣ በድርጅቶች ዘንድ አለ ተብሎ የሚገመተውና በአዲሱ የገንዘብ ኖት በሦስት ወር ውስጥ መለወጥ የሚገባው ገንዘብ መጠን 62 ሚሊዮን ብር ያህል እንደሆነ ለዚሁም በጠቅላላው ተቋቁመው በሚገኙ 2062 የመለወጫ ጣቢያዎች የባንክ ሰራተኞች ሕዝቡን ለማስተናገድ ባላቸው ኃይል ተሰልፈዋል።

**(አዲስ ዘመን ዓርብ ጥቅምት 5 ቀን 1969 ዓ/ም)**

### ከደብዳቤዎች

### ለፀሐይዋ እርዳታ ነው?

በአዲስ አበባ ትላልቅ ጎዳናዎች ላይ ያሉት አንዳንድ መብራቶች ብዙ ጊዜ እንደማያቸው 24 ሰዓት ሙሉ ይበራሉ። ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ድረስ ጭለማ በመሆኑ መብራት ያስፈልጋል።

**የቀኑ መብራት ደግሞ ለፀሐይዋ እርዳታ ነው?**

**ከታዛቢ**

**(አዲስ ዘመን የካቲት 16 ቀን 1972 ዓ/ም)**

### ይታሰብበት

በወንጂ ሸዋ ሲኒማ ቤቶች ከሚታዩት ፊልሞች አብዛኛዎቹ ጆሊጃኪዝምን የሚያንጸባርቁ፣ ጎጂ ልማዶችን የሚያስፋፉ ናቸው። በተለይ አሁን የምርትና የባሕል እድገት ዘመቻ በምናካሄድበት ወቅት እነዚህን ትግል አዘናጊ ፊልሞች ማሳየቱ ተገቢ አይመስለኝም። ይህ አይነቱ ጥቆማ ቀደም ሲልም በተደጋጋሚ የቀረበ ቢሆንም አሁንም እንዲታሰብበት ጥቆማ አቅርቤአለሁ።

**ተማሪ ያደታ ገመዳ**

**(አዲስ ዘመን የካቲት 16 ቀን 1972ዓ/ም)**

# ዓለም አቀፍ

## በሱዳን እስር ቤት በመሰበሩ የቀድሞው ፕሬዚዳንት አልበሽር እጣ ፋንታ አልታወቀም ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቀድሞ ፕሬዚዳንት አል በሽር የታሰሩበት እስር ቤት ተሰብሯል፤ የፕሬዚዳንቱ እጣ ፋንታ አልታወቀም ተብሏል።

ከሱዳን ኮበር እስረኞች ማምለጣቸውን ተከትሎ የቀድሞ ፕሬዚዳንት አል በሽር ጉዳይ አወዛጋቢ ሆኗል። የደጋሎ ፈጥኖ ደራሽ ኃይል የሱዳን ጦር እስረኞችን አስገድዶ ከእስር ቤት እንዲወጡ አድርጓል ሲል ይከሳል። የሱዳን ጦር በበኩሉ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ የእስር ቤት ፖሊሶችን በማስገደድ እስረኞች እንዲወጡ አድርጓል ሲል የቀረበበትን ክስ አይቀበልም።

የቀድሞ የሱዳን ፕሬዚዳንት አልበሽር ታስረውበት የነበረው ኮበር እስር ቤት ተሰብሮ እስረኞች መውጣታቸውን ተከትሎ የፕሬዚዳንቱ ጉዳይ አወዛጋቢ ሆኗል። እስር ቤቱ የተሰበረው በሱዳን ጦር እና በጄኔራል ሀምዳን ደጋሎ በሚመራው ፈጥኖ ደራሽ ኃይል መካከል ግጭት መቀስቀሱን ተከትሎ ነው።

አንድ የሱዳን ሚዲያ እንደዘገበው በሰሜን ካርቱም በሚገኘው የኮበር እስር ቤት ዙሪያ ግጭት መከሰቱን እና በርካታ እስረኞች መለቀቃቸውን ዘግቧል። አንድ በትዊተር የተሰራጨ ቪዲዮ ነጭ ዩኒፎርም የለበሱ እስረኞች በኮበር እስር ቤት ዙሪያ ወደላው መንገድ ሲወጡ ታይተዋል። አል ዐይን ኒውስ የቪዲዮውን እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አልቻለም።

የቀድሞ ፕሬዚዳንት አልበሽርን ጨምሮ በርካታ አመራሮች በሚገኙበት የኮበር እስር ቤት ዙሪያ ግጭት ሲፈጠር አል ቡርሃን እና ዳጋሎ ከተጋጩ ወዲህ ይህ የመጀመሪያ አይደለም። ነገር ግን በትናንትናው ዕለት በእስር ቤቱ ዙሪያ የተካሄደው ግጭት ብዙ እስረኞች እንዲወጡና በሱዳን የተፈጠረው ግጭት እንዲባባስ አስተዋፅዖ አድርጓል።

በርካታ እስረኞች መውጣታቸው በተለያዩ ቪዲዮዎች ቢሰራጩም፣ የአል በሽር እጣ ፈንታ ግን እስካሁን አልታወቀም። አል በሽር ተለቋል፤ አልተለቀቀም የሚሉ እርስ በእርስ የሚጋጩ ሪፖርቶች እየወጡ ነው።

የደጋሎ ፈጥኖ ደራሽ ኃይል የሱዳን ጦር እስረኞችን አስገድዶ ከእስር ቤት እንዲወጡ አድርጓል ሲል ይከሳል።



የሱዳን ጦር በበኩሉ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ የእስር ቤት ፖሊሶችን በማስገደድ እስረኞች እንዲወጡ አድርጓል ሲል የቀረበበትን ክስ አይቀበልም።

የሱዳን ጦር፣ የደጋሎ ኃይል ከእስር ቤት በተጨማሪ የሱዳንን ስትራቴጂክ የአገልግሎት ተቋማትን ማጥቃቱን ገልጿል ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው።



## የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት የአውሮፓ ሀገራት መከላከያቸውን ለማጠናከር እንዲጣደፉ አድርጓቸዋል ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት የአውሮፓ ሀገራት መከላከያቸውን ለማጠናከር እንዲጣደፉ አድርጓቸዋል ተብሏል፡፡

ከሦስት አስርተ ዓመታት በፊት የቀዝቃዛው ጦርነት ካበቃ በኋላ የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት በአውሮፓ ከፍተኛ ዓመታዊ የወጪ ወይም ጭማሪ መታየቱ ተነግሯል።

የዓለም ወታደራዊ ወጪ ባለፈው ዓመት በክብረ-ወሰን ማደጉን የግጭት እና የጦር ትጥቅ ጥናት ባለሙያዎች አስታውቋል።

የዓለም ወታደራዊ ወጪ በፈረንጆች 2022 በሦስት ነጥብ ሰባት በመቶ ወይም በሁለት ነጥብ 24 ትሪሊዮን ዶላር ከፍ ብሏል ሲል የስቶክሆልም ዓለም አቀፍ የሰላም ምርምር ኢንስቲትዩት አስታውቋል።

ለዓመታት እየጨመረ የመጣውን ውጥረት ተከትሎ ባለፈው ዓመት የካቲት ወር የጀመረው የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት የአውሮፓ ሀገራት መከላከያቸውን ለማጠናከር እንዲጣደፉ አድርጓቸዋል ተብሏል። ሞስኮ “ጠላት እና ጠበኛ” ካለችው የምዕራቡ ዓለም ራሷን ለመከላከል “ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ” ያለችውን እርምጃ ወስዳለች።

ዩክሬን እና ምዕራባውያን አጋሮቿ ደግሞ ሞስኮ “ግዛትን ለመንጠቅ ያለመ ጦርነት” እያካሄደች ነው ብለዋል። በዋነኛነት በሩሲያ እና በዩክሬን ጦርነት ምክንያት የአውሮፓ ወታደራዊ ወጪ በ13 በመቶ ጨምሯል ተብሏል።

በአህጉሪቱ ውስጥ ያሉ በርካታ ሀገራት በውጥረቱ ምክንያት ወታደራዊ በጀቶችን እያሳደጉ እና ለመጠናከር እቅድ ማውጣታቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

# ስፖርት

## የማራቶን ፈርጦቹ ወርቃማ ዘመን እያከተመ ይሆን?

ብርሃን ፈይሳ

በተለያዩ የዓለም ከተሞች ከሚካሄዱ የማራቶን ውድድሮች በሚያስተናግዱት ከፍተኛ ፉክክር የኦሊምፒክና የዓለም ሻምፒዮናን ያህል ግምት ከሚሰጣቸው መካከል አንዱ የሆነው የለንደን ማራቶን ነው። የፕላቲኒየም ደረጃ ካላቸው ስድስቱ ዋና ዋና ማራቶኖች አንዱ የሆነው የለንደን ማራቶን ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ የዓለም ሻምፒዮኖችን ጨምሮ የዓለምን ክብረወሰን የማሻሻል አቅም ያላቸው ምርጥ የርቀቱ አትሌቶች ተፎካክረውበታል። እጅግ ተጠባቂ የሆነው ይህ ውድድር የዘንድሮ አሸናፊዎች ከተጠበቀው ውጪ አዲስ ፊት ይዞ ብቅ ማለቱ አስደናቂ ክስተት ሆኗል።

በውድድሩ ለአሸናፊነት ተጠባቂ ከሆኑት ታዋቂና የማራቶን ልምድ ካላቸው አትሌቶች ይልቅ አዳዲስ አትሌቶች የተሻለ ሆነው መገኘታቸው አስገራሚው ክስተት ነበር። በሁለቱም ጾታዎች ከዚህ ቀደም ማራቶን ላይ ልምድ የሌላቸው አትሌቶች በለንደን ማራቶን ደረጃ ባሉ ሩጫዎች አሸናፊ መሆናቸው በእርግጥም አስገራሚ ነው። በመም ውድድሮች አድናቆትን ያተረፈችው በትውልድ ኢትዮጵያዊት በዜግነት ደግሞ ሆላንዳዊት የሆነችው ሲፈን ሐሰን በሴቶች በኩል ባለድል ሆናለች። በወንዶች ደግሞ የግማሽ ማራቶን ልምድ ያለውና ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ባለፈው ዓመት የሮጠው ኬንያዊ አትሌት ኬልቪን ኪፕተም የማራቶንን የዓለም ሁለተኛውን ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ ጭምር አሸናፊ ሆኗል።

የዓለም ከዋክብት አትሌቶች በተካፈሉበትና በተለይ በቅርቡ ከመም ወደ ጎዳና ሩጫዎች የተሸጋገሩ ብርቱ አትሌቶች ተሳትፏቸውን ባረጋገጡበት በዚህ ውድድር ተሳታፊ መሆን በእርግጥም አሸናፊ የሚሆነውን አትሌት ለመገመት አዳጋች ያደርገዋል። ሆኖም በወንዶች በኩል እንደነበረው ሩጫ ከሆነ ቀነኒሳ በቀለን የመሰለ ትልቅ አትሌት መሳተፉ ፉክክሩን አስቀድሞ ሊያከረውና የአሸናፊነት ቅድመ ግምቱንም ሊያስገኝለት እንደሚችል አያጠራጥርም። ሆኖም በውድድሩ የታየው እንዲሁም ከሳምንት በፊት በተከናወነው ሌላኛው ትልቁ ውድድር ቦስተን ማራቶን የተስተዋለው ሁኔታ በማራቶን ለዓመታት የዘለቀው የኃያላኑ የበላይነት ወደማብቂያው ደርሶ ይሆን የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል።

በተለይ ከመም እስከ ጎዳና የዘለቀው የሁለቱ አትሌቶች ጠንካራ ፉክክር እንደ ለንደን ያሉ ትልልቅ ማራቶኖችን በየዓመቱ ተናፋቂ ሲያደርጋቸው ቆይቷል። ማራቶንን ከአንድ ሰዓት በታች የመግባት ተደጋጋሚ ጥረት ያደረገው ኬንያዊው አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ እና በመም የረጅም ርቀት ውድድሮች የነገሰው ኢትዮጵያዊው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ የሚፋለሙበት መድረክ በእርግጥም በስፖርት ቤተሰቡ እጅግ ተጠባቂ ነው። በሰከንዶች የሚሰላው ልዩነታቸውም ይበልጥ የሚጠብበት ውድድር ሲናፈቅ የቆየ ቢሆንም፤ የአትሌቶቹ ወቅታዊ አቋም ግን ከዚህ የራቀ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው። ለማሳያነትም በሳምንት ልዩነት ኪፕቾጌ በቦስተን ማራቶን ስድስተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቁ እንዲሁም ቀነኒሳ የለንደን ማራቶንን አቋርጦ መውጣቱን ማንሳት ይቻላል።

በሴቶች በኩልም ከመምና ከግማሽ ማራቶን ውድድሮች ወጥተው ማራቶንን ከሁለት ዓመት ወዲህ የተቀላቀሉ አትሌቶች የቀደመ ብቃታቸውን ከአዲስ መንፈስ ጋር ይዘው ወደ ውድድር ገብተዋል። የለንደን ማራቶን አሸናፊዋን ሲፈን ሃሰንን ጨምሮ፣ አልማዝ አያና፣ ያለም ዘርፍ የኋላው፣ ገንዘቤ ዲባባ፣... የመሳሰሉ ብርቱ አትሌቶች ከዚህ በኋላም በጠንካራ ፉክክር በረጅሙ ርቀት ሩጫ የሚታዩ አትሌቶች ናቸው። በመም ውድድር ድንቅ አትሌቷ ጥሩነሽ ዲባባም በሳምንቱ መጨረሻ በጃፓን በተካሄደ ግማሽ ማራቶን ውጤታማ መሆኗም ቀጣይ ማረፊያዋ ይኸው ርቀት ስለመሆኑ ጠቋሚ ነው። እንደ አጠቃላይም ከዚህ በኋላ የሚኖረው የማራቶን ሩጫዎች ድል በእነዚህ አትሌቶች ሊመዘገብ እንደሚችልና ምናልባትም አዲስ የማራቶን ምዕራፍ እየመጣ ስለመሆኑ ማሳያ ይሆናል።

ከጥቂት ወራት በኋላ በቡዳፔስት የሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ለዚህ መልስ ሊሆን እንደሚችል እርግጥ ነው። በዚህ ሻምፒዮና ላይ ሃገራቸውን የሚወክሉ አትሌቶችን አሰላለፍም ከወዲሁ ለመገመት ያስችላል። በመም የሚታወቁ አትሌቶች በመሰል ሜጀር የማራቶን ውድድሮች መታየታቸው ምናልባትም በማራቶን ሊወዳደሩ ስለማቀዳቸው ፍንጭ ሊሆን ይችላል። ባለፉት ሻምፒዮናዎች የተሻሉ የነበሩ የርቀቱ አትሌቶች ደግሞ በአዳዲስ ተፎካካሪዎች የሚፈተኑበት ጊዜ መድረሱን የሚያመላክት ይሆናል። በመልካም ወቅታዊ አቋም ላይ ያሉትና በቅርቡ ኦሊምፒክን የተቀላቀሉት እንደ ሞ ፋራህ ያሉ አትሌቶች መጪው የማራቶን ተሳትፎም በቅርቡ የሚለይም ነው።




**የማራቶን ፈርጥ የሆኑት ቀነኒሳ በቀለና ኢሉድ ኪፒቾጌ በአዳዲስ ኮከቦች እየተተኩ ነው፣**


## የጨረታ ማስታወቂያ

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት የጎፋ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ለጎፋ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የሚሆን የህንፃ መሣሪያዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ በግልጽ ጨረታ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ ከዚህ በታች የጠቀሱትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች እንድትወዳደሩ እንጋብዛለን፡፡

1. በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው፡፡
2. በዘርፉ የንግድ ምዝገባ ወረቀት ያለው፡፡
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ የሆነ፡፡
4. የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር (TIN)ያለው፡፡
5. የአቅራቢነት የምዝገባ ወረቀት ማቅረብ የሚችል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተመሰከረለት ሲፒኦ (CPO) ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች ከላይ ከ1-6 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር በማያያዝ በታሸገ ፖስታ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ዘወትር በመንግሥት የሥራ ሰዓት ማስገባት ይቻላል፡፡
8. የጨረታ ሰነዱን ብር 100 (አንድ መቶ ብር) በጎፋ ዞን ገቢዎች መምሪያ በመክፈል ከጎፋ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ቢሮ ቁጥር 4 ያገኛሉ፡፡
9. የጨረታ አሸናፊው ያሸነፋቸውን ዕቃዎች በራሱ ወጪ እስከ ሳውላ ከተማ ጎፋ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ንብረት ክፍል አምጥቶ በጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ ከተፈተሸ በኋላ ማስረከብ የሚችል፡፡
10. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ሲሆን የጨረታ ሣጥኑ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚያኑ ቀን 3፡30 ሰዓት ጨረታው ይከፈታል፡፡ 16ኛው ቀን በዓል ወይም ቅዳሜና ዕሁድ ከሆነ በሚቀጥለው ቀን ይከፈታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

-መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

-ለተጨማሪ ማብራሪያ፡- የስልክ ቁጥር፡- 046 777 1623 ይደውሉ፡፡

**በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት የጎፋ ዞን ፋይናንስ መምሪያ**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በ2015 ዓ.ም ለሚ/አ/ከ/ዋ/ማዘጋጃ ቤት የድሃ ድሃ መኖሪያ ቤቶች አገ/ት የሚውል በጨረታ አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት በጨረታ መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. በጨረታው የሚሳተፉ በSME የተደራጁ ማህበራት መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች በተሰማሩበት የሥራ መስክ የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና የታደሰ ንግድ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የአቅራቢነት ምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የታደሰ ብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 43,700 (አርባ ሶስት ሺ ሰባት መቶ ብር) በጥሬ ገንዘብ/በባንክ በተረጋጠ ሲፒኦ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች ከግብር ነፃ መሆናቸውን የሚያረግጥ ከገቢዎች ጽ/ቤት ማስረጃ ቫት ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱ ሞልተው ሲመልሱ ቴክኒካሉን 1 ኦርጅናል 2 ኮፒ ፋይናንሻሉን 1 ኦርጅናልና 2 ኮፒ በተለያየ ፖስታ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
9. ተጫራቾች የሥራውን ሙሉ ዝርዝር የያዘ የጨረታ ሰነድ በግዥ ንብረት አስ/ር ኬዝ ቲም ቢሮ በመቅረብ የማይመለስ 600 (ስድስት መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
10. ጨረታው የሚከፈተው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ21 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ ቆይቶ በ22ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ታሽጎ በዛው ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ላይ የሚከፈት ሆኖ 22ኛው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን 4:00 ሠዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
11. በተጨማሪ የጨረታ ሰነዱ ክፍል ሶስት ላይ የተቀመጡት ዝቅተኛ መመዘኛ መስፈርቶች የጨረታ ማወዳደሪያ አካል ተደርጎ ይወሰዳል።

**ማሳሰቢያ:-**

-ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ለመግዛት ሲመጡ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ኮፒና ኦርጅናል ይዘው መምጣት አለባቸው።

-ተጫራቾች ሰነዱን ሞልተው ወደ ጨረታ ሳጥን ለማስገባት ሲመጡ ተመዝግበውና ፈርመው ማስገባት አለባቸው፡፡

-መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 047 336 01 24**

**የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት**